

የመንበረ ፀባኦት ቅድ ስት ሥላሴ ካቴድራል ።

ዋጋው [illegible]

# ትንሣኤ



አዲስ አበባ የምትገኘው የመንበረ ንግሥት ቀስቋም ቤተ ክርስቲያን።

ቁጥር ፭፩

ታኅሣሥ ፲፱፻፸፯ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ፣ሥርዓትና ዜና፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብህ ፤
ም በለጠ አበበ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማ ው ጫ

**አርእስት ፤** — **ገጽ**


ደብዳቤዎች ........ ፩
የክርስቶስ ልደት የሰላምና የአንድነት መሠረት ነው ........ ፪
ቅዱስ ሲኖዶስ ጠቃሚዎች የሆኑ ውሳኔዎችን አስተላለፈ ........ ፬
መድኀን ተወልዶላችኋል ........ ፭
ክቡረ ልደት ........ ፯
የግብርና በረከት ........ ፰
በእግዚአብሔር ፊት የምቆም እኔ ገብርኤል ነኝ! ........ ፱
የመምሬ ሙላቱ አስፋው አጭር የሕይወት ታሪክ ........ ፲፩
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፲፪
የመምህር ገብረ ማርያም ይመር አጭር የሕይወት ታሪክ ........ ፲፬
የአዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ ፲፮
ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ........ ፲፮
ከኢትዮጵያ ቅዱሳን ታሪክ ........ ፳
የሴቶች እድር ........ ፳፩
የጨጓራ ሕመም ........ ፳፫


## ደብዳቤዎች

ለተወዳጁ ትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

እንኳን ለአዲሱ ዘመን ከድርጅቱ ሠራተኞች ጋር በሰላም አደረሳችሁ እያልኩ የማቀርባቸውን ጥያቄዎች በመጽሔቷ እንድታወጡልኝ በተስፋ እጠባበቃለሁ።

፩ኛ ግሸን ማርያም የሚገኘው ባለብዙ ታሪኩ መጽሐፈ ጤፉት ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ታትሞ ሁሉም እንዲያነበውና እንዲያውቀው ለምን አይደረግም?

፪ኛ በሰበካ ጉባኤ ከእኛ ዘንድ ስላልከፈላችሁ ሙሉ ገንዘብ ክፈሉ አለዚያ የመቃብር ቦታ አንሰጥም እያሉ የቃለ ዓዋዲውን ውሳኔ ተግባራዊ እንዳይሆን የሚጥሩ ካህናት አሉ ስለዚህስ የተወሰደ እርምጃ አለ ወይ ?

፫ኛ ሰው ሲሞት ለ12 ቀን ብር 10 ለ፴ ቀን ብር ፲ ለ፵ ቀን ብር 2 እህል ውሃም ሳይቀር የሚያስከፍሉ አሉ ታዲያ ሰበካ ጉባኤ ክፍያ ከዚህ ሁሉ ነፃ የማያደርግ ከሆነ አለመክፈሉ ይሻላል ? ወይስ መክፈሉ ?

፬ኛ በየአብያተ ክርስቲያኑ ለሕንፃ ማሠሪያ ገንዘብ ሰብስበው ምንም የተጀመረ ሥራ የማያሳዩ ይገኛሉ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በአንዳንድ አድባራትና ገዳማት ገንዘብ በካርኒ ከፍለን ስናበቃ ገንዘቡም ጭጭ እነርሱም ጭጭ ብለዋል ። ለዚህስ መፍትሔው ምንድነው ?

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን ከበደ

አዲስ አበባ

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን ከበደ በቅድሚያ ስላቀረቡልን መንፈሳዊ ሰላምታ እናመሰግናለን ። እርስዎንም እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ አደረስዎ እንላለን ።

ቀጥለን ላቀረቡልን ጥያቄዎች መልሳቸውን እናቀርባለን ። የመጀመሪያው ጥያቄ ግሸን ማርያም የሚገኘው መጽሐፈ ጤፉት ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ መላው ሕዝብ እንዲያነበው ለምን አይደረግም የሚለው ነው ።

ለዚሁ ጥያቄ አስፈላጊውን መልስ ለማግኘት የግሸን ማርያምን ደብር አስተዳዳሪ መምህር ተክለ ማርቆስ ብርሃኑን ጠይቀናቸው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውናል ።

መጽሐፈ ጤፉት የተባለው መጽሐፍ የተጻፈው በግዕዝ ቋንቋ ስለሆነ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲታተም ከታሰበበት አያሌ ዓመታት አልፈዋል፡ ቀደም ሲል ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ለሊቃውንቱ ክፍል ቀርቦ ተመርምሮ አልቆ ወደ ማተሚያ ቤት ገብቶ ነበር ። ነገር ግን በመካከሉ ላይ አንዳንድ ችግሮች በመፈጠራቸው ከሕትመት ሊዘገይ ችሏል ።

ከደረሱትም ችግሮች አንዱ የገንዘብ ዕጥረት በመሆኑ ከበጎ አድራጊዎች ገንዘብ እየጠየቀ የሚሰበስብ ኮሚቴ ተቋቁሞ አሁን ገንዘብ በመጠየቅ ላይ ይገኛል ። በገንዘብ በኩል ያለው ችግር ከተወገደ መጽሐፉ በቅርብ ቀን ታትሞ ምእመናን እንደ ሚያነቡት ተስፋ እናደርጋለን ። ሲሉ የደብሩ አስተዳዳሪ ገልጸውልናል እንግዲህ ጠያቂውም ከመምህሩ የተሰጠውን መልስ መሠረት በማድረግ በትዕግሥት ይጠባበቁ እንላለን ።

ሁለተኛው ጥያቄ በሰበካ ጉባኤ ተመዝግበው አስተዋጽኦ የሚከፍሉ ምእመናን ሲሞቱ ከእኛ አጥቢያ አልተመዘገባችሁምና አናስቀብርም የሚሉ ካህናት አሉ በእነርሱ ላይ ምን እርምጃ ተወስዶአል የሚል ነው በሰበካ ጉባዔ ተመዝግቦ አስተዋጽኦ ቢከፍልም በይከፍልም ማንኛውም ክርስቲያን መቃብር አይከለከልም ካህናቱም ቢሆኑ መቃብር ሊከለክሉ አይችሉም ካህናቱ ቢጠይቁም ፍትሐት ፍቱ ተብለው የተጠየቁ እንደሆነ ሟቹ በሰበካ ጉባዔ ተመዝግቦ አስተዋጽኦ ያልከፈለ ከሆነ የአገልግሎት ዋጋ ይጠይቃሉ ። ከዚህ ሌላ ስመ ክርስትና ያለው ሰው ሲሞት መቃብር በፍጹም አይከለከሉም የከለከሉ ካሉ ጠያቂው ገልጸው ይጻፉልን የሚመለከተው ክፍል ሕጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል ።

ሦስተኛው ጥያቄ ሰው ሲሞት ለ፲፪ ቀን ብር አሥር ለ፴ ቀን አሥር ለ፵ ቀን ብር ፪ ከእህል ውሃ ጋር የሚያስከፍሉ አሉ የሰበካ ጉባኤ ክፍያ ከዚህ ሁሉ ነፃ የማያደርግ ከሆነ አለመክፈሉ ይሻላል? ወይስ መክፈሉ? የሚል ነው ።

በሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦ አስተዋጽኦ ሲከፍል የኖረ ምእመን በሞተ ጊዜ በአሥራ ሁለት በሰላሳና በአርባ ቀን የሚፈታው በነፃ ነው ለመሥዋዕት የሚሆን ብር ፪ት ብቻ ይጠየቅ እንደሆነ እንጂ ሌላ ሊጠየቅ አይገባም እህል ውሃም ቢሆን ወደው በፈቃዳቸው ካላመጡ በስተቀር እህል ውሀ አምጡ ብሎ የሚጠይቅ ካህን የለም አምጡ ብለው የሚያስገድዱ ካህናት ካሉ ጠያቂው ቢጠቁሙን ለሚመለከተው ክፍል እናስተላልፋለን ።

አራተኛው ጥያቄ በየአብያተ ክርስቲያኑ ለሕንፃ ማሠሪያ ገንዘብ የሚሰበስቡ አንዳንድ ኮሚቴዎች የሰበሰቡትን ገንዘብ በሥራ ላይ እንደማያውሉት የሚጠቁም ነው ።

ጠያቂው ያቀረቡት ጥያቄ ጥሩ ነበር ነገር ግን ለሕንፃ ማሠሪያ ገንዘብ ተዋጥቶ ሲያበቃ ሥራ ሳይሠራ የቀረበትን ደብር ቢጠቅሱልን ኖሮ የአሠራር ጉድለት ያሳየውን ክፍል ለመጠየቅ ይቻል ነበር ።

በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተቋቋሙት የእድሳት ኮሚቴዎች የመዓልቱን ሐሩሩ የሌሊቱን ቁር ሳይፈሩ ከቤተ ክርስቲያን በመገኘት ከበጎ አድራጊዎች ምእመናን ገንዘብ እየሰበሰቡ የፈረሰውን እያሠሩ ያረጀውን እያሳደሱ ያልተሠራውንም እየሠሩ መሆናቸው የተረጋገጠ ነው ።

ከዚህም ሌላ ዕቃ ቤትና ቤተ ልሔም የስብከተ ወንጌል አዳራሽና ደወል ቤት ያልነበራቸው ሁሉ አሠርተዋል በማሠራትም ላይ ይገኛሉ ይህ ሁሉ የእድሳት ኮሚቴዎች የሥራ ፍሬ ነው ።

ይህ ሁሉ ሥራ እየተሠራ የሕንፃ አሠሪዎች ኮሚቴዎች መመስገን እንጂ መነቀፍ አይገባቸውም ነገር ግን አንዳንድ ኮሚቴዎች ከሕዝበ ክርስቲያኑ የሰበሰቡትን ገንዘብ በሥራ ላይ ያላዋሉ ካሉ የተመደቡበትን መንፈሳዊ ሥራ በማከናወን የሥራ ፍሬያቸውን ለሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲያሳዩ በዚህ ጥያቄ መልእክታችንን እናስተላልፋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

## ርዕሰ አንቀጽ

# የክርስቶስ ልደት የሰላምና የአንድነት መሠረት ነው

አዳምና ሔዋን ለመላው የሰው ልጆች መገኛዎች እንደመሆናቸው ለደስታም ሆነ ለኀዘን ምክንያቶች ስለ ሆኑ ችግራችንም ሆነ ደስታችን በምናስታውስበት ጊዜ እነርሱን መጥቀስ ግድ ይሆንብናል ።

ቅርንጫፍ ያለ ግንድ ሊገኝ እንደማይችል እኛም ያለ እነርሱ ለመገኘት አልቻልንምና ደስታቸው ደስታችን ኃዘናቸውም ኃዘናችን ነው አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩ በኋላ እጅግ በጣም አስደሳች በሆነችው ምድረ ገነት እን ዲኖሩ ከእግዚአብሔር ተፈቅዶላቸው ነበር ።

በምድረ ገነት የሚገኘውም ሀብት ሁሉ በጠቅላላው ለእነርሱ ተሰጥቷቸው ነበር ፡ ከዚህም የተነሳ እንስሳትና አራዊት ወደ እነርሱ እየሄዱ አርዳችሁ ብሉን ፡ አልባችሁ ጠጡን እያሉ ሲጠይቋቸው አዳምና ሔዋን እኛ ምን አጥተን እግዚአብሔር አምላክ ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ያለውን ሀብት ሁሉ እንድንጠቀምበት ፈቅዶልናል እናንተንስ በዚያው ባላችሁበት ያርባችሁ ያስባችሁ እያሉ በመመረቅና ስም በማውጣት ያሰናብቷቸው ነበር ዘፍ. ፪፥፳ ።

በዚያን ጊዜ ተንኮልና ክፋት ምቅኝነትና የመሳሰሉትም የማይታወቁ ስለነበሩ ፍጥረታት ሁሉ በሰላም ፡ በፍቅር ፡ በአንድነት ይኖሩ ነበር እንጂ በመካከላቸው ጠብ አልነበረም በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሁድ ተፈጥሮ ሲ ያበቃ የፈጣሪውን ትእዛዝ በመተላለፍ ከመአረጉ የወደቀው፣ከክብሩም የተዋረደው ሳጥናኤል በእባብ ላይ አድሮ ተንኮል በመሥራት አዳምንና ሔዋንን ከምድረ ገነት አስወጥቶ ለማባረር ስለፈለገ ከፈጣሪያቸው ጋር ሊጣሉ የሚችሉበትን የተንኮል መንገድ ይፈልግ ጀመር ።

እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በምድረ ገነት ባስቀመጣቸው ጊዜ በገነት ውስጥ የሚበቅሉትን አትክልት አዝርዕትና የእንጨት ፍሬዎች እንዲመገቡ ሲፈቅድላቸው በገነት ውስጥ ከሚገኙት እንጨቶች መካከል የአንዲን ዕንጨት የበለስ ፍሬ እንዳይበሉ አዘዛቸው ፤ ከዚያች ከተከለከለችው በለስ ፍሬ ቢበሉ የሞት ሞትን እንደ ሚሞቱ ነግሯቸው ነበር ዘፍ. ፪፥፲፯ ።

አዳምና ሔዋን ከፈጣሪ የተሰጣቸውን ትእዛዝ አላከበሩም በዲያብሎስ ቃል እየተመሩ እንዳይበሉ እግዚአብሔር አምላክ የከለከላቸውን የእንጨት ፍሬ ቀጥፈው በሉ ፡ እንደነርሱ አስተሳሰብ ከነበራቸው ደስታ የበለጠ ደስታ እናገኛለን መስሏቸው ነበር ፡ ግን እንኳን የበለጠ ደስታ ሊያገኙ የነበራቸውንም ደስታና ክብር ተነጥቀው ምድረ ገነት ተባረሩ ።•

የደረሰባቸው ኀዘን እጅግ በጣም ከባድ ስለነበር ችግራቸውን ለማቃለል ወደሚችለው ፈጣሪ ከመጮህና ከማልቀስ በስተቀር ሌላ መፍትሔ አላገኙም እግዚአብሔር አምላክ ርኅሩኅና ቸር በመሆኑ ኀዘናቸውንና ልቅሶታቸውን ሰምቶ አምስት ሺ. አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጆቻቸው ተወልዶ ተሰቅሎና ሞቶ እንደሚያድናቸው ተስፋ ሰጣቸው ።

አዳምና ሔዋን ከተባለው ዘመን ለመድረስ አልቻሉም እነርሱን ዓረፍተ ዘመን ቢከለክላቸውም ተስፋውን ሰምተው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ከእነርሱ በኋላ በየጊዜው የተነሡ ነቢያትም ስለ ክርስቶስ መወለድና ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት ትንቢት እየተናገሩ አልፈዋል ክቡር ዳዊት "እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥም አገኘነው" ሲል ተናግሯል መዝ. ፻፴፩፥ ፮ ከልደተ ክርስቶስ ቀደም ብሎ በ፯፻ ዓ.ዓ. ተነሥቶ የነበረው ኢሳይያስ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች በያዕቆብ ቤትም ለዘለዓለም ይነግሣል በጨለማ የሄደ ሕዝብ ታላቅ ብርሃንን አየ በሞት ጥላ ለነበሩም ብርሃን ወጣላቸው ። ሕፃን ተወልዶልና ልና ወንድ ልጅም ተሰጠን አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ ተብሎ ይጠራል መካሪም ብርቱም አምላክ የዘለዓለም አባት ፡ የሰላም አለቃ ፡ መንግሥቱም ይበዛል ፡ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም ብሏል ትን. ኢሳ. ፯፥፲፬፥ ፱፥፪ ።

ሚልክያስ የተባለው ነቢይም አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ ምድር ፣ ከይሁዳ ገዥዎች ብትበልጭ እንጂ ከቶ አታንሽም ሕዝቤን እሥራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወለዳልና በማለት ተናግሯል ትን. ሚክ. ፭፥፪ ።

ለማስረጃ ያህል ጥቂቶቹን ጠቀስን እንጂ የተነገሩት ትንቢቶች እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት አይደለም ሐዋርያው ጳውሎስ "የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድ ልጁን ላከ ከድንግል ማርያምም ተወለደ ብሎ እንደተናገረው የተነገሩት ትንቢታት ይፈጸሙ ዘንድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ዘር ከድንግል ማርያም ተፀነሰ ፣ እንደተፀነሰም ገና ሳይወለድ ከንጉሡ አውግስጦስ ቄሣር ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ የሚል ጥብቅ የሆነ ትእዛዝ ስለተላለፈ ሁሉም ሰው ለመመዝገብ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ከተማ ይጓዝ ጀመር ።



ዮሴፍና ድንግል ማርያም ከዳዊት ወገን ስለነበሩ ለመመዝገብ ከናዝሬት ተነሥተው የዳዊት ከተማ ወደ ሆነችው ቤተ ልሔም ሄዱ ፡ ቤተልሔምም እንደደረሱ ቦታው ሁሉ በእንግዶች ተሞልቶ ስለነበር ማደሪያ ሊያገኙ አልቻሉም ፣ በዚህም ምክንያት ከላሞች በረት ተጠግተው ማረፍ ግድ ሆነባቸው በዚያም እንዳሉ ድንግል ማርያም የመውለጃዋ ቀን ስለደረሰ በመንፈቀ ሌሊት ክርስቶስ ተወለደ በጨርቅም ጠቅልላ በበረት አስተኛችው በበረቱም የነበሩት አህያና ላም በትንፋሻቸው አሟሟቁት ።

በተወለደበትም አካባቢ ብርሃን ሆነ ብርሃኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማየት የበቁት መንጋቻቸውን በንቃትና በትጋት ሲጠብቁ የነበሩት እረኞች ናቸው ። ከዚያ በፊት አይተውት የማያውቁትን ብርሃን በሌሊት በማየታቸው እጅግ በጣም ደነገጡ ፈሩ ፡ ወዲያው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተገልጾ እነሆ ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ይህም ምልክት ይሆንላችኋል ሕፃኑን በጨርቅ ተጠቅልሎ በበረት ተኝቶ ታገኙታላችሁ አላቸው ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ እረኞቹም ስለሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ ሉቃስ ፪፥፩።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ የታየው አዲስ ነገር በተወለደበት ዙሪያ ብርሃን ማንጸባረቁ ብቻ አልነበረም ከዚህ ሌላ ተራሮች ኅብለተ ሕይወት ሆነዋል የዱር እንጨቶችም የበረከት ፍሬን አፍርተዋል የባሕር ውሃዎች ወተትና ማር ሁነዋል ፡ ሰብአ ሰገል ወርቅ ዕጣንና ከርቤ አምጥተው አበርክተዋል ላምና አህያ በትንፋሻቸው አሟሙቀውታል መላእክትና እረኞችም በአንድነት ሆነው አመስግነውታል ይህ ሁሉ የሚያስረዳው በክርስቶስ ልደት መለያየት ተወግዶ አንድነት ፡ ጥል ክርክር ችግር መከራ ተወግዶ ፡ ሰላም ፍቅር ደስታ መመሥረቱን ነው ።

ሰብአ ሰገል ለክርስቶስ ልደት ያቀረቡትን አምኃ ተመልክተናል ስለዚህ የክርስቶስን በዓለ ልደት በምናከብርበት ጊዜ ደከመን ካገኘነው ገንዘብ አውጥተን የተራቡትን በማብላት የተጠሙትን በማጠጣት የተራቆቱትን በማልበስ እንደ ሰብአ ሰገል መደሰት ይገባናል ፡ ሰማያውያን መላእክትና ምድራውያን ሰዎች በአንድነት ሆነው ክርስቶስን እንዳመሰገኑ ሁላችንም በመካከላችን ያለውን ቂም ፡ በቀል ፣ ጥላቻ ፡ ምቀኝነት ፈጽመን አስወግደን በአንድነት በመሆን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም የተወለደውን ክርስቶስ በማመስገን በዓሉን ማክበር አለብን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የሰላም መሠረት ፡ የደኅንነት መገኛ ፡ የአንድነትና የፍቅር መግለጫ ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሲኖዶስ ጠቃሚዎች የሆኑ ውሳኔዎችን አስተላለፈ


በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ መንበርነት የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ከጥቅምት ፲፱-፳፱ አጽድቆ ያስተላለፋቸው ፣

፩ኛ / ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ

፪ኛ በአምስቱም የካህናት ማሠልጠኛ ዳንድ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ውሳኔዎችን አስተላልፎአል ።

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል፡

ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው እየተሰበሰበ



የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በሥራ እንዳሉ

ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ድረስ ባደረገው ስብሰባ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጠቃሚዎች የሆኑ ውሳኔዎችን ። ያስተላለፈ መሆኑ ከቅዱስ ሴኖዶስ ጽ/ቤት ተገልጿል ።

ይኸውም ቅዱስ ሴኖዶስ በውሳኔ ዎች የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች አንድ እንዲሆኑ የሚል ሲሆን በሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን ስለሚያስተምሩ መምህራን በመምሪያው በኩል ተጠንቶ በቀረበለት ጉዳይ ተወያይቶ አጽድቆአል። ከነዚህም ሌላ በአን የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ለቅድስት ቤተክርስቲያናችን እጅግ በጣም ጠቃሚዎች በመሆናቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚተላለፉትን ውሳኔዎች እየተቀበሉ በሥራ የመተርጐም ግዴታ አለባቸው ።



# መድኅን ተወልዶላችኋል

መድኅን ማለት አዳኝ ወይም መድኀኒት ማለት ሲሆን ይህም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ቤዛ ስለሆነ ቀደም ብለው ነቢያት ትንቢት ሲናገሩለት ቆይተው ነበር ከዚህም የተነሳ መድኅን የተባለው ቃል ለረጅም ዘመናት በተስፋ ሲጠበቅ የኖረ ስለነበረ በተፈጸመ ጊዜ ሁሉ ነገር ታደሰ ። የዳዊት ከተማ በነበረችው በቤተልሔም የዘመኑ ፍጻሜ ደርሶ መድኀኒትነቱ በነቢያት የተነገረለት መድኅን ክርስቶስ በመወለዱ ከመርገም በታች ወድቆ ይኖር የነበረውም የሰው ልጅ ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋገረ ። በኀጢአት አርጅቶ የነበረው አሮጌው ዓለም መልኩን ለውጦ አዲስ ሆነ ። ከዚህ በፊት ተደርጎ የማያውቀውና ወደፊትም ሊደረግ የማይታሰበው እረቂቅ ምሥጢር በመገለጹ የሰማይ መላእክትና በሌሊት መንጋቸውን አስማርተው ይጠብቁ የነበሩት እረኞች "ሰላም በምድር እርቅም ለሰው ልጅ ይሁን " እያሉ በህብረት ዘመሩ ። ለሰው ልጆች ታላቅ ደስታና ሰላም ተፈጽሟልና ።

ይሁን እንጂ መድኅን ክርስቶስ ከመወለዱና ለሰው ልጆች ይህን የመሰለው ታላቅ ደስታና ሰላም ከመገኘቱ በፊት የነበሩ አንዳንድ የአረማውያን ገገርዎች እርሳቸውን ማዳን ሳይሆንላቸው መድኅን የተባልን እኛ ነን ለራሳቸው የህሊና እረፍትና የልብ ሰላም ሳያገኙ ለሌላው ሰላም እናስገኛለን እያሉ የተወለዱበትን የልደት ቀን ያከብሩና ያስከብሩ ነበር ።

ያልተማረውና ዕውቀት ያነሰው ህዝብ የተናገሩት እውነት እየመሰለው ሰላም ያስገኙልናል መድኅኖቻችን እነሱ ናቸው በማለት የተወለዱበት ቀን በሚከበርበት ጊዜ የተሠረ ለምለም ቄጤማ የዘንባባ ቅጠል ፣ የወይራ ዝንጣፊ ሲያቀርብላቸው እቅፍ አበባ ሲያበረክትላቸው ኖሮአል ። ከታሪክ እንደምንረዳው ከፈርዖኖች መካከል የተወለደበትን ቀን ሲያከብር ያደረገውን እንመልከት "በሦስተኛው ቀን ፈርዖን የተወለደበት ቀን ይከብር ነበረ ለሠራዊቱም ሁሉ ግብር አደረገ የጠጅ አሳላፊዎቹን አለቃና የእንጀራ አበዛዎችን አለቃ በአሽከሮቹ



ክርስቶስ በላሞች በረት እንደተወለደ

መካከል ከፍ አደረገ የጠጅ አሳላፊዎችንም አለቃ ወደ ሥፍራው መለሰው ጽዋውንም በፈርዖን እጅ ሰጠ የእንጀራ አበዛዎችንም አለቃ ሰቀለው" ኦሪት ዘፍጥረት ም. ፵ ቁጥር ፳-፳፪ መድኅን ነኝ ለሕዝቡ ሰላም እሰጣለሁ እያለ የሚመካው ፈርዖን የተወለደበትን ቀን በሚያከብርበት ጊዜ አስረኛን በመፍታት ለተበደለው ይቅርታ በማድረግ ፋንታ እንጀራ አሳላፊውን ሰቅሎ የወፎች ምግብ እንዲሆን አደረገው ። በዘመኑም የፍርድ ጉድለትና አድልዎ የርስ በርስ መሊያየት ስለነበር በሕዝቡ ዘንድ ሰላም አልነበረም ሰባት ዓመትም ታላቅ ረኀብ ሆኖ በህዝብ ዘንድ ታላቅ ችግር በመድረሱ መድኅን የተባለው ቃል



www.ethiopianorthodox.org

በተግባር ሳይተረጎም ቀርቶአል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የገሊላ ገገር የነበረውን የሄሮድስን ታሪክ የተመለከትን እንደሆነ የተወለደበት የልደቱን በዓል በሚያከብርበት ቀን ለተራቡት ሳይሆን ለመኳንንቱና ለመሳሰሉት ታላቅ የምሳ ግብዣ አደረገ ። በግብዣውም መካከል የዘፈነችው ዘቅኝ ስላስደሰተቸው የጠየቀችውን ሊሰጣት ተስፋ ሰጣት እሷም የባህታዊውን የመጥመቁን የዮሐንስን እራስ ቆረጦ እንዲሸልማውት ጠየቀችው ። ግብዙ ሄሮድስም ልዩ ልዩ የጌጥ ሽልማት ሊሸልማትና የገንዘብ ስጦታ ሊያደርግላት ሲገባው ፍርድ የሚጠባበቀውን የእስረኛውን የዮሐንስን እራስ ቆርጦ ሸለማት የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፬ ከቁ. ፭-፲ ።

ይህን የመሰለውን ግፍ በመፈጸሙ ልደቱ የሰላም የጤንነት የክብር ልደት መሆኑ ቀርቶ የስቃይ ልደት ሆነ ። በህዝብም ዘንድ ሰላም ፍቅር ጠፍቶ መለያየትና ሁከት ተፈጠረ ሄሮድስም መድኅን መባሉ ቀርቶ ግፈኛ ነፍስ ገዳይ የሚለውን ስም ትቶ አለፈ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የተወለደው ለተራበው ዓለም እንጀራ ሆኖ ለመቅረብ ነው ። እራሱ ድኃ ሆኖ ድሆችን ባለጸጋ ለማድረግ ነው ይህንንም ለመፈጸም አምላክና ጌታ ሲሆን በከብቶች በረት ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ልብሱ እሣት እየተባለ የሚነገርለት እሣተ መለኮት በጨርቅ ተጠቅልሎ በግርግም ተኛ ይህንንም በማድረጉ የሰው ፍቅር አገብሮት ለሰላምና ለፍቅር መምጣቱን በተግባር አስመሰከረ ።

ካቢር የተባለው ፈላስፋ ስለ ክርስቶስ ሰው መሆንና መወለድ የሚከተለውን ተናግሮአል "በወንዝ ዳር ሁለት ካህናተ ጣዖትን አገኘ ሰማይና ምድርን ዓለማትን የፈጠረ አንድ አምላክ እያለ ለምን እናንተስ ብዙ ጣዖትን ታመልካላችሁ ሕዝቡንስ በነሱ እንዲያመልክና እንዲያምን ለምን ታደርጋላችሁ ቢላቸው እኛና አባቶቻችን ሲወርድና ሲዋረድ በመጣው መሠረት ስናምን የቆየ ነው በብዙ አማልክት እንጂ በአንድ አምላክ አይደለም አሉት ነገሩን ባትገነዘቡት ነው እንጂ ፀሐይ እስኪወጣ ድረስ ጨረቃና ከዋክብት እንደ ፀሐይ ሙሉ ብርሃን ሰጥተው ሊያበሩና ሊሞቁ አይችሉም ። ስለዚህ እናንተ የምታመልኩዋቸው ጣዖታትም የሱ ስነ ፍጥረትና ሰው ሰራሾች ስለሆኑ የሰውን አዕምሮ ከማጨለም በቀር እንኳንስ ለሌላው ብርሃን መስጠታቸው ቀርቶ ለ





ሰብአ ሰገል ወደ ክርስቶስ እጅ መንሻ ይዘው ሲጓዙ



ራሳቸው ብርሃን የላቸውም እንደ ፀሐይ ብርሃን የሚሰጠውና ፀጋ የሚያድለው እውነተኛው አምላክ ወደፊት ሰው ሆኖ ይወለዳል መድኅንም ሆኖ ዓለምን ሁሉ ያድናል እሱም በተወለደ ጊዜ ጣዖታት ሁሉ ይጠፋሉ ሲል ትንቢት ተናግሮ ነበር ትንቢቱም ተፈጽሞ እውነተኛ መድኅን የሆነው አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ።

ኢሳይያስም እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች። አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ሲል ትንቢት የተነገረለት አማኑኤል በተወለደ ጊዜ ጣዖታት ይጠፋሉ ሲል ተንብዮ ነበር ። ትንቢቱም የሚለው የሰው ኩራቱ ይወድቃል በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል ጣዖቶቻቸውም ሁሉ ፈጽመው ይጠፋሉ በዚያም ቀን ሰው ይሰግድላቸው ዘንድ ያበጃቸውን የብሩንና የወርቁን ጣዖቶቹን ለፍልፈልና ሌሊት ወፍ ይጥላሉ ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፲፯-፳።

እንዳለውም መድኅን ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ በከንቱ ይመለኩ የነበሩት ጣዖታት ሁሉ ጨርሰው ጠፉ ስላዚህም ወንጌላዊው ሉቃስ በጻፈው ወንጌል እንደምንረዳው "እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኅን እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ይህም ምልክት ይሆንላችኋል ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ" በማለት መልአኩ ለእረኞቹ እንዳበሠራቸው ሉቃስ ምዕራፍ ፪ ከቁ. ፰-፲፪ ይናገራል ።

ዛሬም ቢሆን ስለ ዓለም ሰላም የተወለደው መድኅን ክርስቶስ አትፍሩ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እያለ በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ይናገራል ዓለም ግን በገዛ እውቀቱና በገዛ ጥበቡ በራሱ ገንዘብና በራሱ ጉልበቱ እየተመካ በክርስቶስ ሰላም አልተጠቀመም ።

ተከታዩን በገጽ ፳፬ ይመልከቱ

# ክቡረ ልደት | በልደት የከበረ |

በመሠረቱ ሰው ከአባት ዘር ከእናቱ ደም ተከፍሎ በማኅፀን ሲዘራ በእግዚአብሔር ጥበብ እስከ አርባ ቀን ድረስ ተሰዕሎተ መልክዕ ይፈጸምለታል ይህም ማለት ሙሉ አካል አግኝቶ ሰው ወደ መሆን ደረጃ ይተላለፋል። ከዚህ በኋላ ግን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ሙሉ በጨለማ ተዳፍኖ በጠባብ ማኅፀን ዓለም ተወስኖ ሲኖር እናቱ የምትመገበውን እትብት እየተመገበ ይቆያል።የበላችው ተጭኖ የጠጣችው አንገዞ እንዳይገድለውም ጠባቂው እግዚአብሔር ስለሆነ ጠባብ ማኅፀን ዓለም ሳይጨንቀው ያለ ምንም ችግር እስከ ልደቱ ቀን ድረስ ይሰነብታል ። እናቱ ግን በሰላም ተገላግላ ልጅዋን እስከአቀፈች ድረስ ምን እንደሚደርስባት ስለማታውቅ ሥጋቷና ጭንቀቷ የከበደ ይሆናል በሰላም ወልዳ ልጇን አንሽው ምጡን ርሽው በተባለች ጊዜ ግን ከቤተሰቦቿ ጋር ለምታደርገው ደስታ መጠን የለውም የሐ. ፲፮-፳፪ ። ዘመድ አዝማዶቿም ተሰብስበው የእርሷን መገላገልና የሕፃኑን ልደት በደስታ ያከብራሉ ሕፃኑም ከጨለማ ወጥቶ ብርሃን ያየበት ከጠባብ ማኅፀን ዓለም ወጥቶ ሰፊውን ዓለም የተመለከተበት የመጀመሪያ ክብሩ ልደቱ ስለሆነ ከልደት የበለጠ ክብር እንደማይኖረው ይገመታል በዚህም መሠረት ክብረ ልደቱን የምናስታውሰው የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ልደት ነው አቡነ ተክለ ሃይማኖት ታኅሣሥ ፳፬ ቀን የተወለዱበትን ታሪክ ለመዘርዘርና የልደታቸውም ክብር በተስፋ ሲጠበቅ የኖረ መሆኑን ለመግለጽ ነው።ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት አባታቸው ፀጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእ ኀረያ ይባላሉ ፀጋ ዘአብ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ የሚቀበላችሁን መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታሳርጉና ታቀርቡ ዘንድ ክብርት ንጽሕት ለሆነችው አገልግሎት መንፈሳዊት ሁኑ ብሎ ቅዱስ ጴጥሮስ በአንደኛ መልዕክቱ በምዕራፍ ፪ በቁ ፭ላይ በተናገረው መሠረት በንጹሕ ክህነት በቅድስና ሕይወት እግዚአብሔርን የሚያገለግል ንጹሕና ጻድቅ ከዚያም አልፎ ቅዱስ የሆነ ካህን ነበረ ቅዱስ ፀጋ ዘአብ የመጀመሪያ ስሙ ዘርዓ ዮሐንስ ሲሆን ቅድስት እግዚእኀረያም የመጀመሪያ ስሟ ሳራ ይባል ነበር ፀጋ ዘአብና እርሷ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን በጸሎተ ተክሊል ከተጋቡ በኋላ ዘካርያስ፡ የተባለው የቅዱስ ፀጋ ዘአብ አባት ከመልካም ጠባይ ጋር መልክ ከደም ግባት አስተባብራ መያዟ ለሥራዋ መትጋቷን በምግባር በሃይማኖት ያጌጠች መሆኗን አይቶና ተመልክቶ ይችስ ጌታ የመረጣት ናት በማለት እግዚእኀረያ ብሏታል።ከዚህ በኋላ በዚህ ስም የምትጠራ ሁናለች ቅድስት እግዚእኀረያና ቅዱስ ፀጋ ዘአብሕገ እግዚአብሔርን በጥንቃቄ ከመጠበቅ ጋር ሰላምና ፍቅር የሰፈነበት ኑሮ የሚኖሩ አንድ አካልነታቸውን በተግባር ያስመሰከሩ በመልካም አርአያነታቸውም የአካባቢያቸውን ሕዝብ ወደ መልካም ኑሮ የሚመሩ ጻድቃን ነበሩ እኒህ ሁለት ጻድቃን አንች ትብሽ በመባባል ጥቂቱ ብዙ እየሆነላቸው የሚደሰቱበት ሀብት ባያጡም በኑሯቸው ውስጥ የሚያሳዝናቸው አንድ ታላቅ ነገር ነበር ። ይኸውም ለተወሰነ ጊዜ መካነው ልጅ በማጣታቸው ነበር ነገር ግን የሚገኘው ከእግዚአብሔር መሆኑን ስለሚያውቁ የተባረከ ዘር እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን ዘወትር በጸሎት ይለምኑት ነበር በተለይም ቅድስት እግዚእኀረያየምታቀርበው ጸሎት አስደናቂ ነበር እንደ ኤልያስ ለእግዚአብሔር ሕግ ትቀና ስለነበር አቤቱ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ሕግህን የሚጠብቅ በሥርዓትህ የሚመራ አንተን የሚፈራ የተባረከ ልጅ ስጠኝ ሕግህን የማይጠብቅ በሥርአትህ የማይመራ አንተን የማይፈሬ ከሆነ ግን ማኅፀኔን ዝጋው እንጂ እንድትሰጠኝ አልፈልግም እያለች ትጸልይ ነበር ሁለቱም ይህንና ይህን የመሳሰለ ጸሎት



www.ethiopianorthodox.org

በማቅረብእግዚአብሔርን እየለመኑ በ ቅዱስ ሚካኤል ቃል ኪዳን አምነው በ ጸሎቱ እየተማፀኑ ዘወትር ለነዳያን ይ መጸውቱ ነበር በቅ/ ሚካኤል አብሣሪነ ት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተጸ ንሰው ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ሲፈ ጸም ታኅሣሥ ሃያ አራት ቀን ተወል ደዋል ። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ፀጋ ዘአብና ቅዱስት እግዚእኃረያ የጸሎታቸውን ፍሬ በማየታቸው እግዚአብሔርን አመስግነዋል ። ነዳያንን ሰብስበው እያ በሉ እያጠጡ ከዘመዶቻቸው ጋራ በቤ ታቸው ታላቅ የደስታ በዓል አድርገዋ ል እኛም በመግቢያው ላይ ክቡረ ልደ ት ለማለት የቻልነው በዚህ ምክንያት ነው ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተመለከ ትነው እኒህ ሁለቱ ጻድቃን እምነታቸ ውን በእግዚአብሔር ላይ አጽንተውበማ ያወላውል ቁርጥ መንፈስ ጸሎታቸውን ከማቅረባቸው የተነሣ የደረሰባቸውን ፈተና በትግዕሥት አልፈው የተመኙ ትን ቅዱስ ዘር እንዳገኙ ተረድተናል ።

ይህንንም ከተረዳን ያንጊዜ ልመና ቸውን ሰምቶ ከመከራ ያዳናቸው የተባ ረከ ዘር የሰጣቸው ልዑል እግዚአብሔ ሔር ዛሬም ያለ ወደፊትም የሚኖር ባሕ ርዩ የማይመረመር መንግሥቱ የማይ ሻር ዘለዓለማዊ ንጉሥና ዘለዓለማዊ አ ምላክ ስለሆነ ዛሬም እንደነ ቅድስት እግዚእኃረያ በእውነት የሚያምኑትን ሁሉ ልመናቸውን ሰምቶ የፈለጉትን እንደሚሰጣቸው ከመከራም እንደሚያ ድናቸው አይጠረጠርም ታዲያ እንዲህ መስጠት መንሳት መግደል ማዳን ሁሉ ን ማድረግ የሚቻለው አንድ እርሱ ብቻ መሆኑ እየታወቀ እጅግ የሚያሳዝነው የአንዳንድ ሰዎች ግብዝነት ነው ለምሳ ሌ በሐሳባቸው የረከሱ ልቡናቸው ባ ለማወቅ የተሸፈኑ ሊራቀቁ ወደው የ ሰነፉ አንዳንድ ሰዎች የሚያደርጉት ን የተመለከትን እንደሆን መክነው ል

ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል

# የግብርና በረከት እርባታ

የተለያዩ እንስሳትን በማርባትና በማድለብ ጠቃሚ ሀብት ለማግኘት እን ደሚቻል በዚህ ዓይነት ሥራ ከተሠማሩ ድርጅቶችና አንዳንድ ግለሰቦች ለመር ዳት ከመቻሉም በላይ በግብርና ሚኒስ ቴር የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ክፍል በየወሩ እየተዘጋጀ በሚወጣው ዜና ግብርና መጽሔት ስለ ዚህ ጉዳይ ተጨባጭ ማስረጃ እየተላለፈ ነው ።

ዜና ግብርና መጽሔት በተለይም ይህ ዓይነት አሠራር በኅብረት የተደራጁ አምራች ገበሬዎች በይበልጥ እየተጠ ቀሙበትና ለሌሎች ምሳሌ እየሆኑ መታ የታቸውን በየጊዜው ለአንባብያን አቅ ርቦአል ።

እኛም በዛሬው ጽሑፋችን ዜና ግብ ርና መጽሔት በነሐሴ ወር ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ዝግጅቱ ሠንጋዎችን በማድለብ ጠቃሚ ሀብት ለማግኘት እንደሚቻል ያቀረበውን ተጨባጭ ዜና በገጽ ፲፩ ላይ፣

የዶሮ እርባታ በማቋቋም ኑሮን ያለ ችግር መምራት የሚቻል መሆኑን በገጽ ፲፭ ላይ ያሠፈረውን ለአንባብያን ለማ ቅረብ ሞክረናል ።

ለሁሉም መጽሔቱ ያሠፈረውን ቃል እንመለከታለን ። ሀ/ በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ በኪዮ ወረዳ የሚገኘው የቀልታ ቀበሌ የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚያካሂደው የሥጋ ማድ ለቢያ ሥራ ሌሎች ገበሬ ማኅበራትን ለዚህ ዓይነቱ ሥራ የሚጋብዝ ጥሩ ምሳሌ ሆኖአል ። ይልና መጽሔቱ ዝር ዝር ሁኔታውን ሲያብራራ ይህ የቅሬታ ቀበሌ የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅ በር ለማድለብ የሚጠቀምባቸው የቀ ንድ ከብቶች በእርሻ አገልግሎት ለመ ስጠት የሚቻሉትን ሳይሆን በእርሻ አገል ግሎት ከፍተኛ አገልግሎት ሲሰጡ ኖረው ጉልበታቸው የደከመና ይሆን የመሳሰሉ ናቸው ብሎአል ።

እንደገና እነዚህን ከብቶች ለማድለብ ምን ያህል ጊዜ እንደሚጠይቅና በምግብ ረገድ ምን ዓይነት መኖ ማቅረብ እንደ ሚቻል ሲገልጽ ከብቶቹ የሚደልቡበት ጊዜ ከ፯ ወራት እስከ ፰ ወራት መሆኑን

አመልክቶ በምግብ ረገድ ሥራው ገና ለሙከራ ተብሎ የተቋቋመ በመሆኑ በሀገር ውስጥ የሚገኝ ድርቆሽ -ሣር) የአገዳ እህሎችና አገዳዎች ቀን የሚሠ ማሩበት በዘመናዊ እቅድ የተያዘ የግ ጦሽ ቦታ መኖሩንና ከዚህ ጋር ጨው እንደሚጨመር አስረድቶአል ።

ዜና ግብርና መጽሔት በእርሻና በከ ብት እርባታ ለተሠማሩ ሁሉ ለሥራ ቸው መጠናከር የሚያበቃ በባለሙያ ዎች የተሰጠ ትምህርት ስለአለበት ትን ሣኤ መጽሔት ጠቃሚነቱን አምኖ ለአንባብያን ያቀርባል ።

በነገራችን ላይ ይህ የማድለብ ሥራ ከምን ተነስቶ ምን ፍሬ አሳየ ? የሚለ ውን መጠይቅ ብናነሳ መልካም ነው ።

አዎ ከመጽሔቱ ለመረዳት እንደሚ ቻለው ማኅበሩ ፳፩ ከብቶችን በብር ፲፭ሺህ ፯፻ ፶፭ አስራ አምስት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ገዝቶ ከላይ እንደተ ገለጸው ፣ ፯ - ፰ ወር ከደለቡ በኋላ በከፍ ተኛ ዋጋ ሸጦአል ።

የሥራ ዋጋ አለው ዋጋው ይገባዋል እንደተባሉት ሁሉ በ፰ ወራት ወይ ም በ፱፻፵ በሚያህሉ ቀናት ውስጥ ባደረ ገው ጥረት ቀበሌ ማኅበሩ የ፳ ሺ ብር ውጤት አሳይቶ በአርአያነቱ በዚህ ዓይ ነት ላልተደራጁ ማኅበራት እንዲተኋለ ፍ ሆኖአል ።

ለ/ የዶሮ እርባታ በዶሮ እርባታ ሥራ ተደራጅተውና ተጠናክረው በምሳሌነት የቀረቡ በየክፍላተ ሀገራት እንደሚኖሩ ግሐድ ነው ። አሁን ግ ን ለማቅረብ የፈለግነው በሐረርጌ ጀብዱ አምራቾች ማኅበር ካለው ሌላው ሥራው ጋር የዶሮ እርባታ ሥራ ጀምሮ ከፍተኛ በሆነ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ መጽሔቱ አብራርቶአል ።

እንግዲህ ወደራሳችን ቤት መለስ

ወደ ገጽ ፲፭ ዞሯል



# በእግዚአብሔር ፊት የምቆም እኔ ገብርኤል ነኝ

ገብርኤል ማለት « አምላክ ወሰብእ እግዚእ ወገብር «ሰውና አምላክ ጌታና ሎሌ ማለት መሆኑ በቅዱሳት መጽሐፍ ት ተጽፎአል። ቅዱስ ያሬድም በድርሰ ቱ « ገብርኤል ብሂል ወልደ እግዚአ ብሔር » ገብርኤል ማለት የእግዚአ ብሔር ልጅ ማለት ነው ሲል ተናግ ሯል ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚ ብሔር እየተላከ ለሰው ልጆች ከሠ ራቸው ታላላቅ ተአምራት ጥቂቶቹን ለማስረጃ ያህል እንመለከታቸዋለን ።



ቅዱስ ገብርኤል ቮቱ ደቂቅን ከእሳት እንዳዳናቸው

እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሁድ መላእክትን ከፈጠረ በኋ ላ በሰጣቸው አእምሮ ተመራምረው ይ ወቁኝ በማለት ተሠወራቸው ከነገደ መ ላእክት የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ የሚ ገኘው ሳጥናኤል ነበርና ከፍ ብሎ ወደ ላይ ዝቅ ብሎ ወደታች ቢመለከት በቦ ታም ሆነ በመዓርግ ከእርሱ የበለጠ ባ ለማየቱ መላእክትን እኔ ፈጠርኋችሁ አላቸው።በዚህ ጊዜ በመላእክት ዘንድ ታላቅ ሽብር ሆነ ወዲያው መልአኩ ቅ ዱስ ገብርኤል «ንቁም በበሀላዌነ እስ ከ ንረክቦ ለአምላክነ» ፈጣሪያችን እስ ከምናገኝ ድረስ በየአለንበት ጸንተን እ ንቁም» በማለት መላእክትን አረጋጋ ቸው ቅዱስ ገብርኤል ይህንን ቃል በመ ናገሩ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱ ስ ክርስቶስን ከድንግል ማርያም መወለ ድ እንዲያበሥር ባለሟልነትን አገኘ ።

በዚህ መሠረት ፭ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ለድንግል ማርያም ጌ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደምትወልድ አብ ሥሯታል ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤ ል ወደ እመቤታችን ድንግል ማርያም ከመላኩ አስቀድሞ ወደ ዘካርያስና ኤ ልሣቤጥ ተልኮ ነበር ዘካርያስ ከሽመ ገለ ሚስቱ ኤልሳቤጥም ካረጀች በኋ ላ ልጅ እንደሚወልዱና የሚወለደው ም ልጅ ለብዙዎች ተድላ ደስታ እን ደሚሆንና መንፈስ ቅዱስንም ተሞ ልቶ እንደሚያድግ አበሠራቸው ቅ ዱስ ገብርኤል ይህንን መልካም ዜና ለማብሠር ከእግዚአብሔር በተላከ ጊዜ ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ የአገልግሎት ተራው ስለነበር ወደ ውስጥ ገብቶ እጣን ሲያጥን ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር ።

ቅዱስ ገብርኤል በዕጣኑ ማሳረጊያ በስተቀኝ ቆሞ ለዘካርያስ ታየው ዘካ ርያስ መልአኩን ባየው ጊዜ በጣም ደን ገጠ ፍርሀትም ያዘው መልአኩም የዘካ ርያስን መደንገጥ ተመልክቶ ዘካርያስ ሆይ/.ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አይዞህ አትፍራ አትደንግጥ ሚስትህ ኤልሣ ቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስ ሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ሰ ላም ይሆንልሃል ። በመወለዱም ብዙዎ ች ደስ ይላቸዋል ልጁም በጌታ ፊት ታ



www.ethiopianorthodox.org

ኀቅ ይሆናልና የወይን ጠጅ የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል በእስራኤል ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል ። እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያዘጋጅ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል ይሄዳል ሲል አበሠረው ። ሉቃስ ፩.፲፯

ዘካርያስ ግን የመልአኩን የቅዱስ ገብርኤልን ቃል አምኖአል ተቀብለውም እኔ ሸምግያለሁ ሚስቴም ኤልሣቤጥ አርጅታለችና ይህ የተናገርከው ነገር እንዴት ሊፈጸም ይችላል ። በእርግጥ እንደሚፈጸምስ በምን አውቃለሁ ።? አለው ቅዱስ ገብርኤልም መልሶ ከእግዚአብሔር ተልኬ መጥቼ ነበር ። ነገር ግን በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንክ ይህ ነገር እስከሚፈጸም ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንደተናገረው ዮሐንስ ተፀንሶ እስከ ሚወለድ ድረስ ዘካርያስ ዲዳ ሆኖ ኑሮ ከተወለደ በኋላ በ፰ተኛው ቀን በቤተ ግዝረት ለልጁ ስም ለማውጣት ዮሐንስ ተብሎ ይጠራ ብሎ በጻፈ ጊዜ አንደበቱ ተፈቶለት ምሥጢር ተገልጾለት የእስራኤል አምላክ ይባረክ ጉብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጓልና ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደተናገረ «በማለት ትንቢት ተናግሯል ። ሉቃስ ፩፡፷፰ ።

ቅዱስ ገብርኤል የዮሐንስን መወለድ ለዘካርያስና ኤልሣቤጥ በተናገረ በ፮ኛው ወር ወልደ ድንግል ማርያም ሄዶ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሣ በድንግልና እንደምትወልድ አበሠራት እርሷም ምድር ያለ ዘር እንዴት እህልን ለማብቀል ሴትስ ያለባል ልጅ ለመውለድ እንዴት ይቻላል ? አለችው መልአኩም " እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም አላት በዚህ ጊዜ ድንግል ማርያም መልሳ "ነይኒ በከመትቤለኒ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ባለችው ጊዜ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ በማኅፀኗ ማርያም ተፀነሰ ተፀንሶም ከተወለደ በኋላ በኃጢአት ያረጀውን ዓለም አድሶ ለመላው የሰው ልጅ የዘለዓለም ነፃነትን አጐናጽፎታል ።

ቅዱስ ገብርኤል የምሥራችን ያበሠረው ክርስቶስ በተፀነሰ ጊዜ ብቻ አልነበረም በቤተ ልሔም በላሞች በረት በተወለደም ጊዜ ላሞቻቸውን በንቃትና በትጋት ለሚጠብቁ እረኞች "ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና "ሲል አብሥሯቸዋል ። ሉቃስ ፪፡፲-፲፩።

እረኞችም መልአኩ እንደነገራቸው የተወለደውን ክርስቶስን ተመልክተው እያደነቁ ተመልሰዋል ። አሁንም ሆነ ወደፊት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በእግዚአብሔር ስም አምነው በቃል ኪዳኑ ለሚማፀኑ ሁሉ የሚያስደስት ዜናን ያሰማቸዋል ።እንዲሁም እንደ እሳት ከሚነድ መከራ ሥጋና መከራ ነፍስም ያድናቸዋል ። በዘመነ ብሉይ ነቢዩ ዳንኤል ለተራበ አንበሳ ምግብ እንዲሆን በቀረበ ጊዜ የአንበሳውን አፍ ዘግቶ ያዳነው ቅዱስ ገብርኤል ነው ። ሦስቱ ወጣቶች ያናንያ ፤ አዛርያና ሚሳኤል እጅና እግራቸውን ታሥረው ወደሚነድ እሳት በተወረወሩ ጊዜ ወደላይ ነበልባሉ ፵፱ ክንድ የሆነውን እሳት አቀዝቅዞ ያዳናቸው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ነው ።

በዘመነ ሐዲስም ቂርቆስንና ኢየሉጣን በብረት ጋን ከፈላ ውሃ በተጨመሩ ጊዜ የፈላውን ውሀ በማቀዝቀዝ ያዳናቸው ይኸው መልአክ ነው ።

የቅዱስ ገብርኤልን ተራዳኢነት በጠቅላላ በጽሑፍ ለማስፈር ብዙ ዓምዶች ን ስለሚጠይቅ ለአሁኑ የተጠቀሱት ይበቃሉ ፤ ግን የተጠቀሱትን ሥራዎቹን በመመልከት ሁሉም በእግዚአብሔር አምኖ በቅዱስ ገብርኤል በመማፀን ከሚታዘዘው መዓት ለመዳን ይችላል።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ፈጣን ነው ፤ ተረዳኢ ነው ፤ አጥፊውን ለመቅጣት አማኙን ለመርዳት ከእግዚአብሔር ይሳካል ቅጣቱም የሚፈጽመው የተቸገረውን የሚረዳውን ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ያገኘ እንደሆነ ነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይወስነዋል ። ከእርሱ ፈቃድ ወጥቶ ምንም ዓይነት ሥራ ሊሠራ ከቶ አይችልም ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ፀሐይ ስትጨልም ፡ ጨረቃ ደም ስትሆን ፡ ከዋክብት እንደቅጠል ሲረግፉ ፡ አዕባን ሲፈተቱ መቃብራት ሲከፈቱ ፡ መሬት ስትገለባበጥ ፡ ሙታን መቃብር ከፈቱልን መግነዝ ፍቱልን ሳይሉ ሲነሡ ፡ ቅዱስ ገብርኤል ክርስቶስን ሰቅሎ ለመግደል የተባበሩትን አይሁድ ሁሉ ለመደምሰስ ሰይፉን መዘዘ ፡ ነገር ግን የአብ ምህረት ፡ የወልድ ፍቅር ፡ የመንፈስ ቅዱስ ቸርነት ፡ በከለከለው ጊዜ ሰይፉን መለስ አደረገና ወደምኩራብ አይሁድ ቢወረውረው የምኩራቡን መጋረጃ ከላይ እስከታች ድረስ ከፍሎ መሬትን ሰንጥቆ ወደታች ገብቷል ። የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ኃያልነትና ፈጣንነት የተረዳው ነቢዩ ዳንኤል እኔም ስናገርና ስጸልይ በኃጢአቴም ስናዘዝ ለእስራኤልም ለወገኖቼ ኃጢአት በእግዚአብሔርም በምላክ ፊት ስለተቀደሰው ስለአምላኬ ተራራ በጸሎቴ ስለምን ገና ሳጸልቴም ስናገር እነሆ ሰው ገብርኤል አስቀድሜ በራዕይ ያየሁት ፈጥኖ እየበረረ መጣ በማታም በሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ «ብሏል ትን. ዳን. ፱ ፳፩

የቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት በዘመን አይወሰንም አሁንም ሆነ ወደፊት በእግዚአብሔር ስም አምነው በቃል ኪዳኑ የሚማፀኑትን ሁሉ ለመርዳት የተዘጋጀ ስለሆነ በእግዚአብሔር ስም አምነን ብንጠራው ቅዱስ ገብርኤል ፈጥኖ በመምጣት ከደረሰብን ችግር ሁሉ ያድነናል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አዲስ የሆነ ድምፅ እንዲያሰማን በእግዚአብሔር አምነን በቃል ኪዳኑ እንማፀን ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ



# የመምሬ ሙላቱ አስፋው አጭር የሕይወት ታሪክ

መምሬ ሙላቱ አሳፋው ከአባታቸው ከአቶ አስፋው አሰኜና ከእናታቸው ከወይዘሮ የሺእመቤት የሻህ እርገጥ በጅባ



መምሬ ሙላቱ እኒህ ነበሩ

ትና ሜጫ አውራጃ በደንዲ ወረዳ ልዩ ስሙ ኢፋ በሺ ከተባለው ቀበሌ በ1926 ዓ.ም. ተወልደው በወላጆቻቸው እንክብካቤ ካደጉ በኋላ ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ አዲስ አበባ መጥተው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የአማርኛና መንፈሳዊ ትምህርት ተከታትለው የዲቁና ማዕረግ ተቀብለዋል ። ዕድሜአቸውም ለአቅመ አዳም እንደደረሰ በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. ወይዘሮ ጥሩወርቅ ወልደሰማያትን በተክሊልና በቁርባን አግብተው ሲኖሩ ጥረህ ግረህ በላብህ ተጠቀም የተባለውን አምላካዊ ቃል በመከተል እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለማስተዳደር የሚችሉበትን ሥራ በመሻት

፩ኛ/ ቀድሞ በገንዘብ ሚኒስቴር ስር ሲተዳደር በነበረው የመርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. በሕትመት ሙያ ተቀጠሩ ።

፪ኛ/ በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. ሴንትራል ማተሚያ ቤት አዲስ እንደተቋቋመ በዚሁ ሥራ በክፍል ኃላፊነት እስከ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ድረስ ሠርተዋል ።

፫ኛ/ ከ፲፱፻፷፯ እስከ ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. ድረስ በሸዋና በቼምበር ማተሚያ ቤቶች ተዘዋውረው ሠርተዋል ።

፬ኛ/ በማተሚያ ቤት ሞያ ባላቸው ሰፊ የሥራ ልምድ የበለጠ ለመሥራት ወደሚችሉበት ታላቁ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በመዛወር ከ፲፱፻፷ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ አገልግለዋል ።

የመምሬ አስፋው በጐ አድራጐትና መንፈሳዊ አገልግሎት

፩ኛ/ መምሬ ሙላቱ አስፋው ከወላጆቻቸውና ከሃይማኖት አባቶቻቸው የወረሱትን እምነት በማሟላት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይና መንፈሳዊ ሰው በመሆናቸው ወደ ሥጋዊ ጥቅም ብቻ ሣያደሉ መንፈሳዊ ሥራን በመከተል በ፲፱፻፷፷ ዓ.ም. የቅስና ማዕረግ ተቀብለዋል ።

፪ኛ/ በጨቦና ጉራጌ አውራጃ በቾ የሚገኘው ሮጌ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በአዲሱ ፕላን ተሻሽሎ ሲሠራ የአገሬውን ሕዝብ በማስተባበርና በማስተማር ቤተ ክርስቲያኑ እንዲሠራ ከፍተኛ ቅስቀሳ ከማድረጋቸውም በላይ በራሳቸው ገንዘብ ሙሉ አልባሳትና መንበር አሰርተው ከመጻሕፍት ጋር አበርክተዋል ።

፫ኛ/ ለአለንጐ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አልባሳትና መንበር አሰርተው ከመጻሕፍት ጋር አበርክተዋል ።

፬ኛ/ ሀ ለበርበሬ ምድር መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

ለ ለቡሣ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን

ሐ ዳንዲ ወረዳ ለቦዳ አቦ ደብር አልባሳትና መጻሕፍት ገዝተው ሰጥተዋል ።

፬ኛ/ አዲስ አበባ በሚገኘው በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሥራ ጉባኤ አባል በመሆንና ትርፍ ጊዜያቸውንም መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት አበርክተዋል ።

መምሬ ሙላቱ አስፋው በዚህ የሕይወት ዘመናቸው በቃል ኪዳን ከተጋቡት ባለቤታቸው ጋር ፀንተው በመኖር 2 ወንዶች ልጆችና ስድስት ሴቶች ልጆች ወልደዋል ።

መምሬ ሙላቱ አስፋው በዚህ ዓለም በኖሩበት ዘመናቸው በሠሩባቸው መሥሪያ ቤቶች ሁሉ በቅን አስተሳሰብ በማገልገል ዘላቂ ዕውቀት ያላቸውና በሥራ አለቆቻቸውም ሆነ በሥራ ጓደኞቻቸው ዘንድ የተመሰገኑና ትሕትና የተመላባቸው እጅግ ተወዳጅ ስመ ጥሩ ሰው ነበሩ ።

መምሬ ሙላቱ አስፋው ባደረባቸው ሕመም በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሲታከሙ ቆይተው ሰው ሆይ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት በተወለዱ በ፶ ዓመታቸው ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ስለሆነ ልዑል እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ለወዳጆቹ ባዘጋጀው ቅዱስ ቦታ ያሣርፍልን ። ለቤተሰቦቻቸውም መጽናናትን ይስጥልን ።

የገነት ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ አብሮ አደግ
የወንድማማቾች ማኅበር



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ባለፈው ጽሑፋችን በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ስለሚያከናውኖአቸው የእጅ ሥራዎች መግለጻችን ይታወሳል ። በዛሬው ጽሑፋችን የምንገልጸው ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ በስተ ሰሜን በምትገኘው መንበረ ንግሥት ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ስለተቋቋሙት የልማት ተግባሮች ነው ።

በመንበረ ንግሥት ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ሁለት የልማት ሥራዎች ተቋቁመዋል ፡ አንደኛ የዘይት መጭመቂያ ፤

ሁለተኛ የዳቦ መጋገሪያ ናቸው ።

ስለተጠቀሱት የልማት ተግባሮች እንዲያብራሩልን የቤተ ክርስቲያኑን ሰበካ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ የሆኑትን ዲያቆን ገብረ ማርያም ወልደ አማኑኤልን ጠይቀናቸው የሰጡን ማብራሪያ የሚከተለው ነው ።

በዚህ መንበረ ንግሥት ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን የዘይት መጭመቂያና የዳቦ መጋገሪያ ተቋቁመው ሥራቸውን በሚገባ የሚያከናውኑ መሆናቸው የተረጋገጠ ነው ። በመጀመሪያ የተቋቋመው የዘይት መጭመቂያው ሲሆን የተቋቋመውም በ1971 ዓ.ም ነው ። ይህ ፋብሪካ በቀን አሥር ኩንታል ኑግ ይጨቃል እያንዳንዱ ኩንታል ፳፫ ሊትሮችን ያስገኛል በአንድ ቀን የሚጨመቀው ዘይት ፪፻፴ ሊትር መሆኑ ነው ።

ለዚህም ተግባር ተመድበው የሚሠሩ ፬ት ሰዎች ሲሆኑ ከእነርሱም የዝማሬ መዋሥዕትና ያቋቋም መምህራን ይገኛሉ ። መምህራኑ ቀን በዚሁ ሥራ ተሠልፈው ሲሠሩ ውለው ማታ ደግሞ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ አቋቋምና ዝማሬ መዋሥዕት ሲያስተምሩ ያመሻሉ ካሉ በኋላ ዲያቆን ገብረ ማርያም ወልደ አማኑኤል ስለ ዳቦ መጋገሪያው ሲያብራሩ ።



የመንበረ ንግሥት ቁስቋም ካህናት በዳቦ መጋገር ሥራ ላይ

የዳቦው መጋገሪያ የተቋቋመው በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ሰኔ ፲፫ ቀን ነው ከተቋቋመ አሁን ሁለተኛ ዓመቱ ሲሆን ፤ ይኸው ዳቦ መጋገሪያ ያለ ማቋረጥ ፳ ሰዓቶች ይሠራል በእነዚህ ሰዓቶች ሰባት ሺህ ዳቦዎችን ያመርታል ለዚህ ሥራ የተመደቡት ሰዎች ፲፮ ናቸው የሚሠሩትም ስምንቱ አንድ ላይ ስምንቱ አንድ ላይ ተመድበው በፈረቃ ነው ።

ሠራተኞቹ ከቀሳውስት ከዲያቆናት ከመዘምራን የተወጣጡ ናቸው ። ሲሉ ዲያቆን ገብረ ማርያም ገልጸውልናል ስለሚገኘውም ጥቅም ሲያብራሩ ፋብሪካዎቹ የተቋቋሙት ትርፍ ለማካበት ሳይሆን ካህናቱ ኑሮአቸውን ለማሻሻል እንዲችሉና የትርፍ ጊዜያቸውንም በከንቱ እንዳያሳልፉ ስለሆነ የሚገኘው ትርፍ የካህናቱን ደመወዝ ችሎ ለቤተ ክርስቲያኑ ንዋየተ ቅድሳት ለማሟላት ይበቃል በተጨማሪም ዕቃዎች በተበላሹ ጊዜ ለማደሻ የሚሆን ገንዘብ ይቀመጣል ። ብለዋል ።

ዋና ጸሐፊው በተጨማሪ ሲገልጹ በዚህ ደብር እጅግ በጣም በርከት ያሉ ሕሙማን ይፈወሳሉ ካህናቱ ድርሳንና ወንጌል አንብበው ጸሎት ጸልየው ሕሙማኑን የሚያጠምቋቸው በወር ውስጥ ፯ ቀናት ሲሆን ይኸውም ከ፳፩-፳፯ ቀን ባሉት ዕለታት ነው ወደፊት ግን ካህናቱ ወሩን በሙሉ ድርሳን እያነበቡ ጸሎት በመጸለይ ሕሙማኑን እያጠመቁ የነፃ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ አስበናል በማለት ተናግረዋል ።

ለወደፊት ስላለው ዕቅድ ዲያቆን ገብረ ማርያም ወልደ አማኑኤል ሲያብራሩ የልማት ተግባር አንድ ጊዜ በተቋቋመበት መንገድ ብቻ ተወስኖ መኖር ስለማይገባው ወደፊት ሁለት ወፍጮዎችን ለማስተከል አስበን ጥናቱ በሚገባ ተጠንቶ አልቋል አሁን ወፍጮችን ለማስተከል በዝግጅት ላይ እንገኛለን ። ወፍጮዎቹ በቅርብ ቀን ተተክለው ሥራቸውን እንደሚጀምሩ ተስፋ እናደርጋለን ። በተጨማሪም በዚሁ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ክሊኒክ ተቋቁሞ ካህናቱ በነፃ እንዲታከሙ በአካባቢው ከሚኖረውም ሕዝብ ቢሆን ገንዘብ የሌለው በነፃ ያለው መጠነኛ ዋጋ እየከፈለ እንዲታከም ታስቦ ጥናቱም ተጠንቶ አልቆ ከውጭ ሀገር እርዳታ ተጠይቆ እርዳታው ተፈቅዷል በቅርብ ቀን እንደሚቋቋምም ተስፋ እናደርጋለን ። በማለት ዲያቆን ገብረ ማርያም መግለጫቸውን አጠቃለዋል ።

ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ ሥርተህ ብላ እያለች የምታስተምረውን ራሷም በሥራ እየገለጸችው ትገኛለች አንተ የሌላ መምህር ራስህን አስተምር ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም ተግባር ቀድማ የምትገኝበትን መንገድ በመቀየስ ላይ ናት ።

አንዳንድ ካህናት ከገጠር ወደ ከተማ ሲገቡ በከተማ ውስጥ ማረስ መቆፈር ስለሌለ በመቀደስና በመዘመር ብቻ ተወስነን የምንኖር ይመስላቸዋል ። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በከተማ የሚኖሩም ከጸሎተ ቅዳሴውና ከማኅሌቱ ጋር በትርፍ ጊዜያቸው ከተግባረ እዱና ከፋብሪካው ሥራ መሳተፍ ይኖርባቸዋል ። እየተሳተፉም ናቸው ።

በየአብያተ ክርስቲያናቱ ተግባረ እዶችና ቀለል ያሉ ኢንዱስትሪዎች ስለተቋቋሙ ካህናት በትርፍ ጊዜያቸው እየሠሩ ኑሮአቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉ ናቸው ።

የመንበረ ንግሥት ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ካህናትን እንደተመለከትናቸው እግዚአብሔር ለአባታችን አዳም "ብላዕ በሐፈገጽከ" ያለውን ቃል እየፈጸሙ ናቸው ። ካህናቱ ዳቦ ሲጋግሩና ዘይት ሲጨምቁ ተመልክተናል። እንደዚህ ደክሞ የሚመገቡት ምግብ ሕይወተ ነፍስ ይሆናል ፡ ሠርቶ መብላት አምላካዊ ትእዛዝ መሆኑን የማያቁ እንዳሉ እንዲያውቁ ያስፈልጋል ።

አንዳንድ ሰነፎች ሰዎች ሠርቶ መብላትን እንደነውር በመቁጠር ሲያጡና ሲቸግራቸው ሠርቶ ከመብላት ይልቅ ስመ እግዚአብሔር በመጥራት ለምኖ መብላትን ይሻሉ ፡

ነገር ግን ሙሉ ጤንነት ያላቸው ሰዎች ለምኖ ለመብላት ከመዘጋጀትና ጊዜን በልመና ለመሸኘት ከመታገል ተቆጥበው ሠርተው የሚመገቡበትን መንገድ ቢቀይሱ ከሁሉ የበለጠ መልካም ተግባር ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ትምህርትን የተማሩ ካህናት ሁሉ ሠርተው ራሳቸውን ችለው ቤተ ክርስቲያንን የሚረዱበትን የልማት ተግባርን አቋቁማለች በማቋቋምም ላይ ትገኛለች ይሁን እንጂ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተቋቋሙት የልማት ተግባሮች አጥጋቢ ውጤት ሊኖራቸው የሚችለው በሥራው የሚመደቡት ካህናት ጠንክረው የሠሩ እንደሆነ ነው ካለዚያ የልማት ተግባሮች መቋቋማቸው ብቻ ዋጋ የለውም ።

እንደመንበረ ንግሥት ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ያሉትን የልማት ተግባሮች ስንመለከት እጅግ በጣም ደስ ይለናል እንደዚህ ያለው የልማት እንቅስቃሴ በቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ብቻ ተወስኖ መቅረት አይኖርበትም ለውሳው አድባራት ና ገዳማት መዳረስ አለበት ።

እንግዲህ ይህንን ጽሑፍ የተመለከቱት የአድባራትና የገዳማት ካህናት ሁሉ የልማት ተግባር አልጀመሩ እንደሆነ እንዲያቋቁሙ አቋቁመው እንደሆነ ደግሞ በንቃትና በትጋት በመሥራት ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ ቤተ ክርስቲያንንም እንዲያበለጽጉ በዚህ አጋጣሚ መንፈሳዊ መልእክታችን እናስተላልፋለን ።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## የመምህር ገብረ ማርያም ይመር አጭር የሕይወት ታሪክ

መምህር ገብረ ማርያም ይመር በወሎ ክፍለ ሀገር በዋድላ ደላንታ አውራጃ የስንዴ ሚካኤል ከሚባል ቦታ በ1898 ዓ.ም. ከአባታቸው ከብላታ ይመር ደስታ ከእናታቸው ከወይዘሮ የምሥራች ወርቁ ተወለዱ ።

መምህር ገብረ ማርያም ይመር 9 ዓመት ሲሆናቸው በአያታቸው በብላታ ወርቁ ወሰን ቤት ሁነው በዚሁ ወረዳ ውስጥ አሲም ተክለ ሃይማኖት ከሚባል ደብር ከመሪጌታ እጅጉ ዘንድ ንባብና ዳዊት የቃል ትምህርትና ጾመ ድጓ ምዕራፍ አጠናቀው ተማሩና ዲቁና ተቀብለው ይቀድሱ ጀመር ከዚያም ደላንታ ውስጥ አባ ነአኩቶ ለአብ ከሚባል ቦታ ከአለቃ ተክለ አቢብ ዘንድ ቅኔ ተማሩ ከዚያም ወደ አማራ ሳይንት ሔደው ባሮ ሚካኤል ደብር ከየኔታ ትኩነህ ዘንድ የቅኔ አገባብን በደንብ አጠናቀው ስለአወቁ በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ከዚያም ወደዙር አንባ ሔደው ከመምህር አምኃ ዘንድ ዝማሬ መዋሥዕት ተምረው ሲያበቁ ወደቤተ ልሔም ሔደው የሰለልኩሳ ቅዳሴን ከየኔታ በዛብህ ተምረው ተመርቀዋል ከዚያም እንደገና ወደ አማራ ሳይንት ተመልሰው የጉድ ማርያም ከአለቃ ሊጋሱ የዜማን ይትበሀልና የውዳሴና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜን በደንብ ተምረው በአፍቀራ ቂርቆስ ደብር ቅዳሴና ንባብ ቅኔ እያስተማሩ ብዙ ዘመን በብሕትውና ከኖሩ በኋላ ወደደብረ ሊባኖስ መጥተው የምንኩስና ማዕርግን ከቆሞስ ዘካርያስ ዘንድ ተቀበሉ ቀጥሎም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የቅስናና የቁምስና ማዕርግ ተቀብለው ወደአማራ ሳይንት ተመልሰው ጥንት ያስተምሩበት ከነበረው ደብር አፍቅራ ቂርቆስ ማስተማር ጀመሩ በዚህ መካከል የአፍቀራ ቂርቆስና የተንጉባለል መድኃኔ ዓለም የወፍ አንጭ ማርያም ደብሮች ካህናት ለመምህርነት ስለመረጡአቸው ካሉበት የሹመት ደብዳቤ መጥተላቸው ብዙ ዘመን እነዚህን በሳይንት የሚገኙ ትን ሶስት ደብተሮች ተሹመው በመምህርነት አስተዳድረዋል ፤ የጠላት ዘመንንም ያሳለፉት በነዚሁ ደብሮች ነው ከዚያ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በባታ መታሰቢያ ቤት በንባብ መምህርነት ተቀጥረው እያስተማሩ በትርፍ ጊዜአቸው ከመምህር ወልደ ሚካኤል ዘንድ በኋላ አቡነ ሚካኤል



መምህር ገ/ ማርያም እኒህ ሀበሩ

ከተባሉት ደብረ ዓባይን ቅዳሴ ከሰረር ኩላው ቅዳሴ ጋር በማመሳከር እንደገና የደብረ ዐባዩን የቅዳሴ ዜማ በመምረጥ አጠናቀው ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ከዚያም በ1938 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ወደ ደብረ ጽጌ ሔደው ከዙር አንባው ከአለቃ መርዓዊ ዘንድ የዝማሬ መዋሥዕት ሞያቸውን እንደገና አስፋፍተው ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። ከዚያም ተመልሰው ግቢ ገብርኤል ከታወቁት ሊቅ ከመምህር ሰይፈ ሥላሴ ዘንድ የመጻሕፍት ሐዲሳትን ትርጓሜ ተምረው በቅድስት ማርያም ውስጥ ላዕከነ አርድዕት ሁነው እንደቆዩ በብፁዕ ቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ የቅድስተ ቅዱሳን ማርያም መምህር ሁነው እንዲሠሩና ቅዳሴ እንዲያስተምሩ ተሾሙ ከዚያም ወደወሎ ክፍለ ሀገር ላስታ አውራጃ የማድሪ ጊዮርጊስ ደብርን የዋሮ ቅ. ሚካኤልን ደብር ተሾሙ ይህ ሁሉ ሲሆን ቅዳሴም እያስተማሩ ነው ከዚያም ብዙ ዘመን ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ ወደአዲስ አበባ ተመልሰውየዝቋላ ገዳም መምህር ሁነው ተሾመው አገልግለዋል ከዚያም ተመልሰው ዳግመኛ የቅድስተ ቅዱሳን ማርያም መምህር ሁነው ተሾሙ በዚህ ጊዜ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ተሳለመው ተመልሰዋል ቀጥለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጠቅላይ ቤተ ክህነት የአስተዳደርና የመንፈሳዊ ዳኛና ጉባዔ አባል ሁነው ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ የጡረታ ዘመናቸው ስለደረሰ የጡረታ መብታቸው ተከብሮላቸው በቅድስት ማርያም የካህናት ቦታ ላይ በከፍተኛ ፲፪ ቀበሌ ፲፩ ውስጥ ቤት ሠርተው ባላቸው የመንፈሳዊ ዝንባሌ የተራበ በማብላት የተጠማ በማጠጣት ዕንግዳ በመቀበል ቅዳሴን ከማስተማር ጋር የመድኃኔ ዓለምንና የእመቤታችን ቅድስት ማርያምን ዝክረ በዓል ከፍ ያለ ዝግጅት እያደረጉ ካህናትን ድኆችን እየጠሩ ይዘክሩና ይመግቡ ነበር ።

መምህር ገ/ ማርያም ይመር የታመመ በመጠየቅ የአዘነ በማጽናናት የተጣላ በማስታረቅ ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ተወዳዳሪ የሌላቸው መልካም አባት ነበሩ መምህር ገብረ ማርያም ይመር ወንድም ወዳጅ ተንኮል ምቀኝነት የሌለባቸው ከሁሉ ጋር ተግባቢ ዕገሌ ትልቅ ነው እገሌ ትንሽ ነው ሳይሉ በትክክል ሁሉንም የሚያከ ብሩ ትሁት ከሁሉ ጋር መግባባት የነበራቸው ቸር አስተሳሰባቸው ሰፊ ሰውን ከሰው ጋር አስተዋዋቂ ከአንደበታቸው ሽንገላና ውሸት የማይወጣቸው ታላቅ ሰው ነበሩ በዚህ ሁኔታ ሳሉ ጥቂት ቀን ከታመሙ በኋላ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ጸበል ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በ፹፯ ዓመታቸው ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. አርፈው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትናኤጲስቆጶሳት ጋር በተገኙበት ኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. በደብረ ሊባኖስ ገዳም የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

የዜናው አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል
ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም



# የግብርና በረከት

ከገጽ ፰ የዞረ

ስንል ዛሬ ቃለ ዓዋዲው በሚያዘው ደንብ መሠረት በየሀገረ ስብከቱ የየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀሩ እንደየቦታው አመችነት የልማት እንቅስቃሴ እየተካሔደ ነው ። በጥሩ እንቅስቃሴአቸውም በምሳሌነት የቀረቡ ብዙ እንዳሉን ደጋግመን አሳውቀናል ።

በተለይ ደግሞ ያሉን የካህናት ማሰልጠኛዎች ለካህናቱ ከሚሰጡት የቀለም ትምህርት ሌላ የሙያ ትምህርትም እንደሚሰጡ እናውቃለን ። ነገር ግን በዜና ግብርና እንደተገለጸው ሁሉ በሬ አድልቦ በጥሩ ውጤት በመሸጥ መጠቀምን ፤ ዶሮ አርብቶ ለአካባቢው ምሳሌ መሆኑን የቱን ያህል አጠናክረው የያዙት ለመሆናቸው ለምስክርነት አልበቃንም

ተሞክሮ ከሆነ መልካም ነው ራስን በራስ ለመርዳት ከሚያስችሉ ዓበይት ነጥቦች መካከል በ8 ወራት የ፭ ሺ ብር ትርፍ ባለቤት ለመሆን መብቃት ታላቅ ምሳሌ ነውና ማሰልጠኛዎቻችን በሬን በማድለብ ዶሮን በማርባትና እንደ ሐመረኖኅ ኪዳነ ምሕረት በላም እርባታ ለወተትና ለሥጋ ከብቶች መብቃት መልካም ነው ።

ይህን ካሳየን በኋላ እንደየአመችነቱ ካሉት ፫ ወይም ፮ ማሰልጠኛዎች መካከል ይህን ዓይነት የማድለብ ሥራ ጀምሮ ነገ በምሳሌነት ሳልተንቀሳቀሱት ክፍሎች ለማቅረብ እንደምንችል በተስፋ እንጠባበቃለን ።

የልማት እንቅስቃሴአችን ከጉጆ እንዱስትሪ እስከ ከፍተኛው የልማት ሥራ ተጠናክሮ ቤተ ክርስቲያናችን ራስዋን በራስዋ ለመምራት የምትችለው ይህ ዓይነቱ ሥራ ከአጥቢያ ቤተ ክምስቲያን ጀምሮ በወረዳ ፤ አውራጃና ሀገረ ስብከት ለመጠናከር ሲችል ነውና የሚመለከተው ክፍል ቢያስብበት መልካም ነው ።

በለጠ አበበ



www.ethiopianorthodox.org

# የአዳዲ ማርያም ቤተክርስቲያን ታሪክ

አዳዲ ማርያም በሸዋ ክፍለ ሃገር በመናገሻ አውራጃ በቀርሣ ወረዳ ውስጥ ትገኛለች ይህች ቤተ ክርስቲያን ከአሉት ድንጋይ ቋጥኝ የተሠራች አስደናቂ ናት ያነፃትም በ፲፩ኛው መቶ ዓ-ም ላይ ነግሦ የነበረው ቅዱስ ላሊበላ ነው፡ ይህችም የቋጥኝ ቤተ መቅደስ ልትሠራ የቻለችው ቅዱስ ላሊበላ ነግሦበት በነበረው ዘመን ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከላዕላይ ግብፅ ንሂሳ ከምትባል ሀገር ተነሥተው በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አክሱም ጽዮን ከደረሱ በኋላወደ ላስታ ሮሃ ሄደው ከንጉሡ ከቅዱስ ላሊበላ ጋር ተገናኙ ላሊበላ ያነፃቸውንም የቋጥኝ አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወሩ ጐበኙ ንጉሡ ላሊበላም መላ አካላቸውን ጠጉር እንደሸፈነውና ገጻቸው በረድኤተ እግዚአብሔር እንደለመለመ ባየ ጊዜ በብዙ አድናቆትና አክብሮት በማስተናገድ ብዙ መንፈሳዊ ነገርን ከተጨዋወቱ በኋላ ንጉሡ ላሊበላ አባቴ ሆይ!አሁን ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በዚህ በሮሃ እንዲቀመጡ ፈቃደኛነዎ አላቸው ጻድቁም እኔ ልቀመጥ የፈቀድኩት በሸዋ ክፍለ ሀገር ውስጥ በደብረ ታቦር አምሳል ከሆነች አንባ ዝቋላ ነው አሉት ንጉሡም የመረጧትን በዓት ለማየት ይፍቀዱልኝ አብሬዎ ልሂድ አለችው እርሳቸውም ፈቀዱለትና አንድ ወር በላይ የሚያስጉዘውን መንገድ በእግዚአብሔር ረዳትነት ከነሠራዊቱ በጥቂት ቀን ሸዋ ውስጥ ኤረር ከሚባለው አንባ ደርሰው ዛሬ ቆፍቱ ላሊበላ ከሚባለው ቤተ ክርስቲያን ላይ ነገራተ እግዚአብሔርን እየተጫወቱ አደሩ ፡ በዚያችም ሌሊት ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የቅዱስ ላሊበላን ሥራና ክብሩን ጌታ ተገልፆ ነገራቸው ይህንም ምሥጢር ገልጸው ለንጉሡ እንዲህ አሉት የእግዚአብሔር ወዳጅ ላሊበላ ሆይ!በዚች ቦታ በስምህ ቤተክርስቲያን በኋላ ዘመን ይሠራበታል ከዚህ ሌላ አዳዲ በምትባል ቦታላይ በላስታ ሮሃእንዳነጽካቸው ያለ ከቋጥኝ ድንጋይ ላይ በእመቤታችን ድንግል ማርያም ስም ቤተ መቅደስ እንድትሠራ ታዘሃል ከዚህ ሥራህ በኋላ ወደ ሀገርህ በቶሎ ተመለስ ምክንያቱም ታላቅ እንግዳ ይመጣብሃልና ነው በጐ ሥራህን ሁሉ እግዚአብሔር ተቀብሎሃል ብለው ነገሩት በማግሥቱም ሠራዊቱ በዚህ በቆፍቱ ላይ እንዲቆዩ ሆኖ ሁለቱ ላሊበላና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በከጥቂት ሠራዊት ጋር ወደዝቋላ አንባ ደረሱ ከዚያም ያችን አንባ ንጉሡ ላሊበላ ተመልክቶ በውነት የደብረታቦር አምሳል ናት የእግዚአብሔር ፈቃዱ ባለመሆኑ ነውእንጅ ከዚች አስደሳች ቦታ አልሄድም ነበር አሁንም አባቴ መንፈሳዊ ሥራዎ የተቃና ይሁንልዎ እርስዎም በጸሎትዎ አይርሱኝ ይህች ቦታ ዳሯ እሳት መሐሏ ገነት ትሁንለዎ ብሎ ደብሮቡራኬ በመቀበል ወደ ታዘዘበት ቦታ ለመሄድ ተመልሶ ከደብሩ ግርጌ የቀሩትን ሠራዊት ጨምሮ ከላይ ስሟ ከተጠቀሰው አዳዲ ደርሶ እየተዘዋወረ ሲመለከት አንዲት አነስተኛ ዋሻ አግኝና ስለ ቦታዋ መመረጥ አደነቀ የቋጥኙ ድንጋይም ለጥ ያለ ሜዳ መረሬና ቀይ ድንጋይ ነበር ልክ በላስታ ሮሃ ፲፩ዱ አብያተ ክርስቲያናት የተሠሩበትን ድንጋይ ይመስላል ከዚህ በኋላ እራሱ ፕላን አውጥቶ ጠቢባኑን ሰብስቦ ከላይ ወደታች እያስቦረቦረና እየፈለፈለ መቅደስ፣ ቅድስት ፣ ቅኔ ማኅሌት፣ ቅጽር በመለየት አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን አነፀ የአከፋፈሉም ዝርዝር ሁኔታ ፳፭ ደረጃዎች ፫በሮች መቅደሱ ፫ ክፍልና በሮች ፱ መስኮት ቅኔ ማኅሌቱ ፳፬ በሮች ቅድስቱ ፫ በሮችና ፫ ክፍል ፱ መስኮቶች በመቅደሱ እራስጌ ከዚያው ከአለቱ ተፈልፍሎ የወጣ አስደናቂ መስቀል የተሰኩ የሰሎን እንቁላሎች በማድረግ ወደ ቤተ ክስስቲያኒቱ ለመግባት የሴትና የወንድ የካህናት መግቢያ ብሎ ፫ በሮች በማውጣት ከዚያው የተከፈለ ቅጽር /ዕድሞ/ በመፈልፈል አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ነው የሠራው ቦታው ሜዳ ነው በሩቅ ሁኖ ቤተ ክርስቲያኑን ሲመለከቱት ምንም ነገር የሌለው ሜዳ መስሎ ይታያል ቀርቦ ለማየት የታደለ ግን በጣም ይደነቃል በአጠገቡ የአዳዲ ወንዝ የተባለ ውሃ በብዛት ይወርዳል አስደናቂና ተአምረኛ ፈዋሴ ድውያን የሆነ የእመቤታችን ጸበል አለ ቤተ ክርስቲያኒቱም በአንፋር ዛፍ የተከበበች ናት አዳዲ ማለትም በኦሮምኛ ቋንቋ አንፋር ማለት ነው ይባላል የውሃ ችግር የለም የህል አይነቶች ፡ ጤፍ ፡ ስንዴ ፡ ገብስ ፡ አተር ፡ ምስር ፡ የመሳሰሉት ይበቅሉባታል ፡ ወደ አዳዲ ማርያም ለመሔድ የመንገድ ችግር የለም ፡ ከአዲስ አበባ እስከ አዳዲ የመኪና መንገድ ተሠርቶአል ርቀቱም ከአዲስ አበባ እስከ አዳዲ 67 ኪሎ ሜትር ሲሆን ከአዋሽ ድልድይ ፲፰ ኪሎ ሜትር ወጣ ብሎ ከመልካ ቆንጥሬ ኩታ ገጠም ነው ፡ አዳዲ ማርያም ከአካባቢዋ ውበት ፡ ከዕፀዋቷ መዓዛ ሌላ ለአዲስ አበባ ቅርብ ስለሆነች ለሀገር ውስጥና ለውጭ ቱሪስቶች ጉብኝት በመች ቦታ ናት የአዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥራ ኢትዮጵያውያን በፈጠራ ጥበብ ውጤት የሚመዘኑበት ታላቅ መመኪያና መኩሪያ ናት አዳዲ ማርያም በላሳታ ሮሃ ለሚገኙት የቋጥኝ አብያተ ክርስቲያናት ምስክር ናት ስመ ጥሩ ጻድቅ ቅዱስ ላሊበላ ይህችን ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ባለች ተወዳጅ ቦታና በተዋበ መልክ በማሳጌጥ ከሠራ በኋላ በአንድ ሽህ አንድ መቶ ፹፬ ዓ.ም ኅዳር ፳፭ ቀን ቅዳሴ ቤቷን አክብሮ ንዋየ ቅድሳትና ለካህናቱ ርስት ጉልት ሰጥቶ ከገደማት በኋላ ወደመናገሻ ከተማው እንደተመለሰ ብዙ ዘመን ሳይቆይ በአንድ ሽህ አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ዓ.ም ሰኔ ፲፪ ቀን አርፎ በቤተ ጐልጐታ ውስጥ ተቀበረ አዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያንም ከዚያ ዘመን ጀምሮ እስከአሁን ድረስ የመፍረስና የዝናብ ፍሳሽ አይገኝባትም ታቦቷም ተአምረኛና ፈጥኖ ሰሚ ሁኖ በመገኘቷ ከፍተኛ የገንዘብና የንዋየ ቅድሳት ገቢ የሚገኝባት ብዙ የውጭ ሀገር ቱሪዝም የሚጐበኞት ታላቅ ታቦት ናት ።

ገድለ ላሊበላንና ሥዕሉን በቤተ መቅደሷ አጽፋና አስላ ይዛ ትገኛለች ምስክሯም ይህ ገድል ነው በአዳዲ ማርያም መስኮቶች ላይ በልዩ ጥበብ የተቀረጸ የላሊበላ ስም ይገኝበታል አዳዲ ማርያም ብዙ መንፈሳዊ ካህናቶችና መናንያን ይገኙባታል ።

ምዕውናና ሆይ ይህችን ታሪካዊ ቦታ ለማየት እንድትችሉ ታሪኳን በአጭር ገልጸናል ሄዶ መጐብኘቱ የአንባቢያን ፋንታ ነው ።

አባ መስቀል ተስፋዬ ዘጉ- ነተ/ማርያም



የአዳዲ ማርያም ቤተክርስቲያን

# ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ

ለዚህ ትምህርት ርእስ ሆኖ የቀረበው ኃይለ ቃል የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል የተናገረው ነው ይኸውም በስድስተኛው ወር በሃያ ዘጠኝ ቀን ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ አንዲት ድንግል ቀርቦ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ካንች ጋር አንድ ይሆናልና ። ብሎ የምስራቹን በነገራት ጊዜ ሰማያዊ ስጦታን የተመላሽ ደስ ይበልሽ ካለ በኋላ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ወይም የተመሰገንሽ ነሽ በማለት የደስታ ምስጋና እንዳቀረበላት ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው ወንጌል በምዕራፍ ፩ በቁጥር ፳፰ ተጽፎ ይገኛል ።

እንግዲህ ከሴቶች ተለይተሽ የሚለው ንባብም ቅድስት ድንግል ማርያም ከሴቶች ፍጹም ልዩነት ያላት መሆኗን የሚገልጽ ነው ሴቶች ልጅ ከወለዱ በኋላ ድንግልና አይኖራቸውም ድንግል ማርያም ግን በድንግልና እግዚአብሔር ወልድን ከወለደችው በኋላ ማህተመ ድንግልናዋ ባለመለወጡ እናትነትና ድንግልናን ሁለቱንም ክፍሎች አስተባብራ ይዛ ተገኝታለች ሌሎች ሴቶች ልጅ ከወለዱ በኋላ እናቶች ይባላሉ እንጂ ደናግል አይባሉም ድንግልና ሥጋም ሊኖራቸው አይችልም እናትነትና ድንግልና ሁለቱም ተቃራኒዎች ሲሆኑ እመቤታችን ድንግል ማርያም ግን በዚህ ዓለም ስምምነት የሌላቸው ሁለት ተቃራኒ ክፍሎች ማለት ወሊድና ድንግልናን አስማምታ እስከ ፍጻሜ ዘመንዋ ይዛ ተገኝታለችና ነው ስለዚህ ከሴቶች ልዩነቷን ቅዱስ ገብርኤል መስክሮአል ። በሌላ በኩልም በድንግልና ሥጋና በድንግልና ህሊና ጸንታ በመገኘቷ በእግዚአብሔር ተመርጣ እግዚአብሔር ወልድን ለመውለድና የአምላክ እናት ለመሆን በቅታ ተገኝታለች ደራሲውም የድንግል ማርያም ህሊናዋ የአምላክ ህሊና ነው በማለት ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን መስክሮአል ይህም አባባል የሚአስገነዝበው ረቂቅ መለኮት ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ስለተዋሀደ ነው በብህንሳ ሀገር ኤጲስቆጶስነት የተሾመ አባ ሕርያቆስ እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን በአመሰገነበት ምስጋና የመላእክት እህታቸው በማን እንመስልሻለን በማለት አመስግኗታል ከሰዎች ይልቅ ምክንያት ኃጢአት የሌለባቸው የረቂቃን መላእክት እህታቸው ናት ብሎ መስክሮአል ። ምክንያቱም በተፈጥሮና በነገድ ሳይሆን በንጽሕና በቅድስና ትመስላቸዋለችና [illegible]ም ሌላ በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከኪሩቤል ትበልጣለች ከሱራፌልም ትበልጣለች በማለት አመስግኗታል እንግዲህ ከቅዱሳን ኪሩቤልና ሱራፌል የምትበልጥ ከሆነ ከፍጡራን ወገን በንጽሕና በቅድስና የሚመስላት እንደሌለ ያስረዳል በሌላ በኩልም ሥጋዋን አንጽቶ እሷንም ቀድሶ አክብሮ ከእሷ ተወለደ ይላል ሥጋዋን አንጽቶ ማለት ቀድሞ በአዳም ምክንያት ብሌት አግኝቶ የነበረውን ሥጋ አንጽቶ ተዋሃደ ማለት ነው ሌሎች ሴቶች ከነቢብና ከገቢር ቢነጹ ከሀልዮ አይነጹም በስም ደናግል ቢባሉም በመከላከልና በመጠበቅ በቦታ ከሰው ተለይተው በመኖርና ከምግብና ከመጠጥ ቀንሰው በመታገሥ በክርስቶስ የገቡትን የቃል ኪዳን ስለፈጸሙ አስበ ድንግልናቸውን ይቀበላሉ ማለት ሰማያዊ ክብርን ይወርሳሉ በስምም ደናግለ ሥጋ ይባላሉ እንጂ ደናግለ ሕሊና አይባሉምና የህሊና ድንግልና የተሰጣት ለቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ነው ከእግዚአብሔር በታች





www.ethiopianorthodox.org

ክርሷ የሚከብር የለም ተብሎ ተጽፎአልና በማማለድም በኩል ከወላጅነቱ እንደሥጋዊ አማላጅነት ያለ አይደለም የድንግል ማርያም አማላጅነት በህፀጸ ሃይማኖት በዓፀደ ምግባር የተያዙትን ከልጅዋ ከወዳጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ እያማለደች የማያልፈውን ሰማያዊ ርስት መንግሥተ ሰማይና ዘለዓለማዊ ክብርን ስታሰጥ ትኖራለችና ዓለምም ባንች ዳነ በልጅሽም ሰላም ሆነ ተብሎአልና የዚህ ዓለም አማላጆች ቢአማልዱ ለጥቂቶች ሰዎች ነው እመቤታችን ድንግል ማርያም ግን ሁሉን ታማልዳለችና እንግዲህ ልንገነዘበው የሚገባ አንድ ነገር አለ ለፍጥረታት ሁሉ ተመሳሳይ ይገኝላቸዋል በቅድስት ድንግል ማርያም ግን ተመሳሳይ አይገኝላትም በንጽሕና በቅድስና የአምላክ እናት ለመሆን በቅታ ተገኝታለችና ክርሷ በቀር ለዚህ ታላቅና አስደናቂ ክብር በቅቶ የተገኘ የለም ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ወልድን በሕቱም ድንግልና ፀንሳ በሀቱም ድንግልና እንድትወልደው ሁናለች በአንድ በቅዱስ ገብርኤልና በአንዲት የዮሐንስ መጥምቁ እናት በሆነች ኤልሣቤጥ ብቻ ተመስግና አልቀረችም ከእንግዲህ ወዲህ ፍጥረቱ ሁሉ ያመስግኑኛል በማለት ራሷ ተናግራለች ስለዚህ የምህረት አማላጅ እንደመሆኗ መጠን የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ስአሊለነ ቅድስት ሳይሏት አይውሉምና ስለዚህ ፀሐይ ከማይደርስበት ደርሳ ትመሰገናለች ተብሎ በታሪክ ይወሳል ፀሐይን ዋሻ ተራራ እልፍኝ አዳራሽ ይጋርዳታል የመቤታችንን ምሥጋና ግን ቦታ አይወስነውም በዋሻ የሚኖሩ ባሕታውያን በየቤተ ጸሎታቸው ዘግተው የሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በጸሎት ሲአመሰግንዋት ይኖራሉና እርሷም ምዕራገ ጸሎት ናትና የምህረት አማላጅነቷን አምነን ለምንማጸናት ሁሉ ዓስበ ጸሎታችንን እንድታሰጠን የታአመነ ነው ።

መ ኪዳነ ማርያም አየለ

## ክቡረ - ልደት

ከገጽ ፰ የዞረ

ጅ ይሰጣል ። እያሉ በሰው ተጠግቶ ለማያኝሩ ሰይጣን ሲሳሉ ይታያሉ መስል ጓደኞቻቸው ደግሞ እግዚአብሔር በባሕርይ ልግሥናው የሰጣቸውን ሕፃናት ልጆቻቸውን ዘንዶ ጠምጣሚ እሸዋ ቃሚ እያለ በሚያጋፍተው በሽተኛ ፊት አቅርበው በእርሱዎ መጀን ተማጽነናል እያሉ በመንበርከክ በሲጋራ ከተቃጠለ ሳንባው የሚወጣ ትንፋሹን እፍ እንዲልባቸው በጫት የተመረዘ ምራቁንም እንዲተፋባቸው እያደረጉ በሽታ ሲያስከትቡ የግፍ ግፍ በልጆቻቸው ላይ ሲፈጽሙ ይታያሉ ከዚህም የበለጠ አሳዛኝ ተግባርና የከበደ ወንጀል ስለሌለ እንዲህ ያሉት ሰዎች በእግዚአብሔር ሕግ ከመቀጣትና ከገሃነም ፍርድ አያመልጡም ።

መልአከ አሚን ዘካርያስ



# ችሮታ ከሰብአዊነት ርኅራኄ የሚመነጭ ልግሥና ነው

“ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ (የተባረከ) ነው” ሲል የዓለም መድኅን ክርስቶስ የተናገረውን የወንጌል ቃል አስታውሱ” ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ (የሐዋ ፤ ፳ ፤ ፴፭) ። ስለዚህም ተቀባይ ከመሆን ሰጪ መሆን ምን ያህል እንደሚያስከብር ማስተዋል አያዳግትም ።

ነገር ግን ሰጪ ከመሆን ይልቅ ተቀባይ ለመሆን የሚያስገድዱ አያሌ ምክንያቶች አሉ ለምሳሌ የጤንነት መታወክ የቦታና ጊዜ አለመመቻቸት የእሳዳጊና ሰብሳቢ ዘመድ ወዳጅ ማጣት (ወዘተ) አንዳንድ ግለሰቦችን የሰው እጅ ተመልካቾች ሆነው እንዲቀሩ የሚያደርግበት ወቅት አለ ። በተለይም በታዳጊ አህጉር ይህ ዓይነቱ ችግር በየጊዜው የዞረ ድምር (ተንከባለል) እየሆነ መምጣቱና በተለይም አብያተ ክርስቲያናትን የብዙ ድሆች መጠለያና መናኸሪያዎች እንደሆኑ ማድረጉ አይዘነጋም ። ምእመናንም ይሆን ሁሉ ችግር ለመቋቋም በምግብም ሆነ በልብስ በገንዘብና ማቴርያል የሚቻላቸውን ችሮታና ልግሥና ከማድረግ የተቆጠቡበት ጊዜ የለም በችግር የተጠቁ ወገኖች ሁልጊዜ የሰው እጅ ተመልካቾች ሆነው እንዳይቀሩ ራስ አገዝ ድርጅት ለመፍጠርም ኅብረተሰቡ መሞከሩ አልቀረም ። ታዲያ ይዋል ይደር እንጂ ይህ ችግር ተወግዶ ሁሉም ሰው አንዱ የሌላው ሸክም ሳይሆን ራሱን መርዳት የሚችልበት የኑሮ ዘዴ እንደሚገኝበት ተስፋ ይደረጋል ።

ይሁን እንጂ ምድር እንኳ ልትሸከመው የማይቻላት ከእርሳስና ከብረት የከበደ ሌላ ችግር ደግሞ አለ ። ያም ችግር ከስንፍና ከዋልጌነትና ከወስላታነት የሚመነጭ ሥራ ጠልነት ነው ። “መሬት ሑሉን ነገር ተሸክማ ስትኖር የሚከብዳት የለም ከሰነፍ ሰው በቀር” ተብሎ የተነገረበትም ምክንያት ይኸው መሆኑ ነው ።

ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ሥራ ጠል ሰነፍና ዋልጌ ሙሉ ጤንነት እያለው እጁን አጥፎ እግሩን አንጥፎ በመዋል ኅብረተሰቡን በልመና ሲያሠለች መኖሩ እጅግ ያሳዝናል አንዳንዱማ ጤንነትና ጉልበት ያለው ከመሆኑ የተነሣ ምጽዋት ሲሰጡት ሲቀርቡ በሥነ ሥርዓት በመቀበል ፈንታ ቀምቶ ለመውሰድ የሚያሳየው ስግብግብነት እያስገረመን ነው ።

አንዳንድ ለጋሦች ምዕመናን ተርፎዋቸውም ሳይሆን ከሰብአዊ ርኅራኄ በመነጨ ክርስቲያናዊ ችሮታ የሚሠነዝሩትን ስጦታ ተቀብለው በአግባቡ በመጠቀም ፈንታ እንደጠላት ንብረት በመቁጠር ብዙ ዋጋ ማውጣት የሚችለውን ልብስም ሆነ ምግብ ለትንሽ ገንዘብ መልሰው በመሸጥ ጠጥተው ሲሰክሩበት ማየትም ሌላው አስገራሚ ነገር ነው ።

በመሠረቱ ልግሥና ከሰብአዊ ርኅራኄ የሚመነጭ እንጂ በሞኝነት የሚገኝ ትርፍ ሀብት አይደለም ። የመስጠት ልምድ ያላቸው ለጋሶች እንኳንስ ሠርተው ያመረቱትን ለምነው ያገኙትን እንኳ መልሰው ሲመጸውቱ ይገኛሉ ። “የጧት ለማኝ ለማታ” እንዲሉ ያሏትን ሁለት ሣንቲሞች ወደሙዳዩ ምጽዋት ስትጥል አይቶ ክርስቶስ ያመሰገናትን የዚያችን የሐዲስ ኪዳን መበለት አርአያና ምሳሌነት በመከተል እንኳንስ ሀብታቸውን ሕይወታቸውን ለወገናቸው አሳልፈው ከመስጠት የማይመለሱ ብዙ ቸሮታ አድራጊዎች አሉ ።

ነገር ግን በተቀባዮች መካከል የሚታየው አንዳንድ ሥራ ጠል ዋልጌነት ልግሥና ከሞኝነት የመነጨ እየመሰለ ልዩ ልዩ አቃቂር ሲያመጡላቸው በመስማት እየሰለቻቸው እጃቸውን እስከመሰብሰብ የደረሱ አይታጡም ለማለት የሚያስደፍር ብዙ ሁኔታ እየታየ ነው ።

አንዳንድ በአስተዳደግ የተበደሉ የሞራል ድሆችማ የልግሥና ስጦታ ሲቀርብላቸው እንደባህላችን መርቆ መቀበል ይቅርና ከነጭርሱ በጉልበታቸው ያገኙት ይመስል እንደአሞራ መንትፈው ወስደው ፊታቸውን ወደሌላ አዙረው ሲበሉ ይታያሉ ። ስድባቸው አሽሙራቸው እንደጋሬጣ የሚቀድ ሐሜታቸው እንደዘርዛራ ማጭድ የሚያጫድ በመሆኑ ባጠገባቸው የሚያልፍ የሚያገድመው ሁሉ ምላሳቸውን በመፍራት እግሩ ተሳስሮበት ሲሰነካከል ይታያል ።

ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ ኢክርስቲያናዊ ሁኔታ አይቻልምና ሰምቶ አይቶ “ጆሮ ዳባ ልበስ” ብሎ ከማለፍ በቀር ሌላ ምርጫ የለም ። ይህም ዓይነቱ የዋልጌዎች ቅጥየለሽ ሥራ በጤንነት ጉድለት ወይም በተፈጥሮ አቅም በላይ በሆነ ሌላ ችግር ውስጥ ያሉትን ወገኖች ለመርዳት የሚዘረጉ የልግሥና እጆችን ሁሉ የሚያስር በመሆኑ መታረም የሚችልበትን ዘዴ መፈለግ ይገባል እንላለን ችሮታ ከፍጹም ሰብአዊ ርኅራኄ የሚመነጭ ክርስቲያናዊ ሥርዓት በመሆኑ እንጂ ራሱ እየተቸገረ ካለው ከእጅ ወደ አፍ ገቢው ከፍሎ ለችግረኞች የሚለግስ ሞኝ በጎ አድራጊ ከቶ የለምና እንደዚህ ያለው አንጀት የሚቆርጥ ዕንባ አድርቅ የሰነፎች አጉል ትችትና አሉባልታስ ቢገታ መልካም ነው ።

ቄ መክብብ አጥናው



www.ethiopianorthodox.org

# ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ታሪክ

ካለፈው የሚቀጥል ፣

ከመጋቢ ስብሐት መልእኩ ፈለቀ

ባለፈው ጽሑፋችን ስለጻድቁ አባ ዮሐኒ ታሪክ በአጭሩ መግለጻችን የሚታወስ ነው ። በዛሬው ጽሑፋችን ደግሞ ስለቤተክርስቲያናቸው አመሠራረትና አቀማመጥ እንገልጻለን ። የአባ ዮሐኒ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ሲሆን ስሙም ደብረ አንሣ (ደብረ ዓሣ) እንደሚባል ባለፈው ጽሑፍ ተገልጿል ።

በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊትና በዙሪያው አሥራ አምስት ጥንታውያን ዋሻዎች ይገኛሉ ። ቤተ ክርስቲያኑም የተመሠረተው በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዓፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት መሆኑን ታሪክ ያስረዳናል ። በቤተ ክርስቲያኑ ጥንታውያን የሆኑ ቅርሳቅርሶች በብዛት ይገኙበታል ቤተ ክርስቲያኑ የአንድነት ገዳም እንደነበር ይነገራል ።

በዚሁ ቤተ ክርስቲያን መግቢያ ላይ እንዳ ኪዳነ ምሕረት የምትባል ሕንፃ ትገኛለች በሕንፃይቱም አጠገብ ድልድል የሚባል ማረፊያ ቦታ አለበት ቤተ ክርስቲያኑ ከገደል መካከል ከገደሉ ላይ ተፈልፍሎ የተሠራ በመሆኑ የገደሉን ርቀት ወደላይና ወደታች ሲመለከቱት ከአምስት ሺህ ሜትር ቢበልጥ እንጂ አያንስም ወደቤተ ክርስቲያኑ የመግቢያ ዋሻ በጣም ጠባብ ነው ።

በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያሉት ዓምደ ወርቆች ከዚያው ከገደሉ የተጠረቡ ናቸው ። ቁጥራቸውም ፴፮ ነው የቤተ ክርስቲያኑ ጠፈር ከገደሉ ደንጊያ እንደጣውላ ተጐርዶ በቤተ ክርስቲያኑ መጠን የተሠራ ሲሆን ከገደሉ ጋር የተያያዘ ነው ። የጉልላቶቹ ርዝመት ፲፪ ሜትር ሲሆን መልካቸውና ቅርጻቸው በትምህርተ መስቀል አምሳል የተቀረጹ ናቸው ። ስፋታቸውም ከስድስት ሜትር ቢበልጥ እንጂ አያንሥም ።

መንበሮቹ ሦስት ናቸው ። የተፈለፈሉትም ከደንጋይ ነው የመካከለኛው መንበር በጣም ከፍ ያለ ነው ። እንደ ገዳሙ ሕግ የበቃ ካህን ይቀድስበታል። እንጂ ማንም ተራ ካህን ቄስም ሆነ መነኩሴ አይቀድስበትም ።

መቅደሶቹ ሦስት ሲሆኑ በጣም ሰፋፊ ናቸው ። በተጠቀሰው መካከለኛ መንበር አቡነ ተወልደ መድኅንና አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቀድሰውበታል ይባላል ።

ቤተ ክርስቲያኑ ጥንታዊ ይሁን እንጂ የተገደመውና ሥነ ሥርዓቱ የተሟላው በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው በዚሁ ዘመን የነበሩት አቡነ እናንያለዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ነግረው አስገድመው ሥርዓቱም እንዲሟላ አስደረጉት ይላል ። በዚያው የሚገኘው ወንጌሉ ዘወርቅ "የአቡነ እናንያም ገድላቸው ከዚሁ ገዳም ይገኛል መጽሐፉ ሌሎችም ታሪኮችና ዜናዎች ስለሚገኙበት በክብር ይጠበቃል ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እጅግ በጣም የሚያስደንቁ ሁለት የአልጋ ሸንኮሮች ይገኛሉ አሠራራቸውም እንደግብፅ ቤተ ክርስቲያን ነው ይባላል ። ቤተ ክርስቲያኑን ከዱሮው አብልጠው ያነጹትና የፈለፈሉት አቡነ አሮን ዘመቄት ናቸው ። በምሥራቅ የቤተ ልሔሙ ሕንፃ የሚገኝ ሲሆን በስተምዕራብ ደግሞ ሦስት ክፍሎች ዋሻዎች አሉ እነርሱም የዕቃ ማስቀመጫዎች ናቸው። ደጃፋቸው ግን አንድ ነው ።

በዓጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት የተሠራ መረዋ ይገኛል ። በቤተ ክርስቲያኑ የተለያዩ አራት ድምፆች ያሏቸው አራት ደወሎች አሉ ። አቡነ ተወልደ መድኅን ይጸልዩባቸው የነበሩ ሁለት ክፍሎች ዋሻዎች በቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ በስተግራ ይገኛሉ ። ከዋሻው ገባ ብሎ የተንቢኖች አባት የኤሉስ መቃብር ይገኛል ።

መነኮሳቱና ያካባቢው ክርስቲያኖች የሚቀበሩት በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ባለው ዋሻ ሲሆን ዋሻው ከጥንት ጀምሮ የተፈለፈለና የተቀረጸ ደንበኛ የሆነ የመቃብር ዋሻ ነው ። ሰው ሲሞት መዝጊያውን እየከፈቱ ከውስጡ ሬሳውን አጋድመው ገጥመውት ይሄዳሉ ። የገደሉ ኃይል ወዲያውኑ ሬሳውን እንደጨው አሟሙቶ እንደውሃ ይመጠዋል። በዚህ ምክንያት አይሸትም ።

የሀገሬው ሕዝብ በየአቅጣጫው በሚገባ የተዘጋጀ የመቃብር ቦታ ስላለው የመቃብር ቦታ ችግር የለበትም ሰው በሞተ ቁጥር የመቃብር ቦታ አይፈለፈልም ፤ ከላይ እንደተገለጸው ቀደም ብሎ የተዘጋጀ የመቃብር ቦታ አለና ፤ ዕንግዳ ሰው በድንገት ሲሞትም የሀገሬው ሕዝብ ከሚቀበርበት ዋሻ ይቀበራል ።

የመነኮሳቱ መኖሪያዎች ስምንት ዋሻዎች ናቸው ። መነኮሳቱ ጸሎታቸውን የሚያደርሱት በሚኖሩበት ዋሻ ነው የሚመገቡትም ከምእመናን በሚያገኙት እስተዋጽኦና አንዳንድ በጎ አድራጊዎች አትርሱኝ እያሉ በሚልኩላቸው የእርዳታ ገንዘብ ነው ።

በአካባቢው የሚኖረውም ሕዝብ ማንም ሳያስገድደው እህልና ገንዘብ እያዋጣ በገዳሙ ለሚኖሩ መናንያንና ለቤተ ክርስቲያኑ መገልገያ ይሰጣል ። የጻድቁ የአቡነ ዘክርስቶስም አጽም በሣጥን ሆኖ ከመቅደሱ ውስጥ ባለው ዋሻ ይገኛል ። ዓፄ ገብረ መስቀል የሰጧቸው ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳት በቤተ ክርስቲያኑ ዕቃ ቤት በሚገባ ተጠብቀው ይገኛሉ ።

የአባ አሞንዮስ መቃብርም በዚያው ይገኛል ። ጻድቁ አባ ዮሐኒ ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ያደጉበት ዋሻ በየወሩ የአባ ዮሐኒ መታሰቢያ በዓል ዕለት እንዲሁም

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



## የሴቶች ዓምድ

ብርሃን ተድላ

# የሴቶች እድር ፡

ይህ በዘመናችን ቢገኝም ቀደም ብሎ በነበረው ዘመን አያቶቻችን ቅድመ አያቶቻችን ኋላም እናቶቻችንና አክስቶቻችን የዝን ቤት በማለት ሲገለገሉበትና ሲረዳዱበት ማኅበራዊ ኑሮ ሲያሳዩበት ኑረዋል ።

እንደ አሁኑ በእድሩ የተመዘገቡ ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ቀድሞ የነበሩት እናቶች በጐረቤታቸውም ሆነ በካባቢያቸው አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ እርዳታውንና አገልግሎቱን ለተጋሩት ቤቶች ብቻ ሳይተው ሁሉም ይተባበሩበታል እርዳታው ግማሾቹ እስከሬኑን ተከትለው ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚጓዙበት ጊዜ እንደአሁኑ [illegible] አውጥተው አስለቃሽ ሳይቀጥሩ ሁሉም አልቃሽና አስለቃሽ በመሆን የሃዘን ግጥም በመግጠምና ሙሾ በማውጣት የተሰበሰበውን ሰው ዕንባ በእንባ ያራጩት ነበር ።

ግማሾቹ ደግሞ በሟቹ ቤት ተገኝተው ለቀስተኛው እስኪመጣ ድረስ ንፍሮ በመቀቀል እንጀራ በመጋገር ወጥ በመስራት በመሳሰለው ሁሉ ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ።?በዚህን ጊዜምንም እንኳን እንደዛሬው ድንኳን ባይኖር የቻለ ዳስ ይጥላል ። ያልቻለም በቤቱ ውስጥ በመቀመጥ ሴቶቹም ያዘጋጁትን በማቅረብና በጠቅላላው በማስተናገድ ይረዳሉ ።

ከዚያም እስከ ሰባት ቀን ድረስ ከየቤታቸው እንጀራውንና ወጡን አዘጋጅተው በማምጣት በእድሜ ገፋ ያሉት ደግሞ ተረት እየተናገሩ ሲያጽናኑና ሲመከሩ ይሰነብቱ ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ከኀዘንተኞቹ ቤት ምንም አይነት ወጭ አይወጣም ነበር ። ያም ሆኖ የሚበላ የሚጠጣ ከመትረፍረፉ የተነሣ ትራፊው ለችግረኞች መርጃ ይሆን እንደ ነበር ። በዕድሜ ካገለገሉት እናቶችና አባቶች ለመረዳት ይቻላል ።

ታዲያ በእዝን ቤት ይደረግ የነበረው የእርስ በርስ መረዳዳትና መደጋገፍ በቤተሰብ መካከል ታላቅ መፈቃቀርንና መተሳሰብን ሲፈጥር ከመቻሉ ሌላ በኀዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ ያለውን አብሮ ተከፋፍሎ መብላት የተለመደ መሆኑን ስንመለከት ምን ያህል ማኅበራዊ ኑሮን መስርተውልን እንዳለፉ ይህ መረጃ ሊሆነን ይችላል ።

በቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በልዩ ልዩ አካባቢዎች የሴቶች ዕድር እየተመሠረተ በተለይም በከተማዎች ተስፋፍቶ ይገኛል ።

ይህም ድርጊቱ የሚፈፀመው በሁለት አይነት ነው ። አንደኛው በወንዶች በኩል ዕድር ቢኖርም የሴት እድርበማቋቋም ሴቶች ተሰብስበው በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ ያዋጣሉ ። የራሳቸውም ሆነ የባሎቻቸው ዘመዶች በሞቱ ጊዜ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚችል እንደ ሽሮ በርበሬና የወጥ እህሎችን የመሳሰለውን አዘጋጅተው ካስቀመጡት ውስጥ አስከሬን ከቤት በወጣ ጊዜም ሆነ በመርዶ ጊዜ እስከ ፫ ቀን ምሳ እራት በማዘጋጀትና በማቅረብ በማስተዛዘንም ሲያገለግሉ ይሰነብታሉ ። ይህንንም በማድረጋቸው ለኀዘንተኞቹ ታላቅ አገልግሎት ስለሚሰጡ ከጥንት ሲያያዝ የመጣውን የወላጆቻችን ባህል ያለቀቀ በመሆኑ የሚደገፍና ማንኛውም ኅብረተሰብ ቢለምደው ጠቃሚ ነው ። ይህንንም ስንል ወጭው መጠነኛ ሆኖ ቤትን ሳይጐዳ የሚሰጠው አገልግሎት ግን ከፍ ያለ በመሆኑ ነው ። ምክንያቱም ያዛምዳል ያቀራርባል በሃዘንም ጊዜ ሆነ በደስታ ጊዜ አብሮ መሥራትንና መደጋገፍን ስለሚፈጥር መተሳሰብን ፍቅርንም ይመሠርታል ።

ሁለተኛው ደግሞ ባወጣጡና በርዳታ አሰጣጡ በኩል የመጀመሪያውን ሲመስል ከዚህ ለየት ያለ ሌላ መልክ ያለው ዕድር አለ ። ይህም ማኅበር አይሉት ወይንም እቁብ በየወሩ አባላቱ በየተራ ታላቅ ድግስ እየደገሱ ማብላት ማጠጣት ሲሆን በድግሱ ላይ ከዳቦው ከቆሎውና ከጠላው ሌላ የማኅበሩ ቀዋሚ ሕግ አለው አንዲት ተረኛ ደጋሽ በአንድና በሁለት ኪሎ የበሬ ስጋ ሳይሆን አንድ ከዚያም በላይ እንደችሎታዋ በግ አርዳ መደገስ ግዴታዋ ሲሆን ሁለትም ሆነ ሦስት ጠርሙስ አረቄ የማይቀር ሲሆን ድግሱ በጾም ጊዜ ከዋለ ደግሞ ወጥ በ[illegible]ይነቱ እንዲሠራ ሆኖ ቲማቲምና ቃሪያ ግን መቅረት የሌለበት ነው ። ድግሱም በአንድና ሁለት አይነት ወጥ ብቻ ሳይሆን ግብዣው ራሱ ብፌ ነው ሕጉም የሚያዘው ይህንኑ ነው ። ታዲያስ ይህ አይነቱ እድር መረዳጃ ወይንስ የቤት ገቢ አቃዋሽ እንዲህ አይነቱን እድር ምን ስም እናወጣለት ? ምንስ ብንለው ይስማማው ይሆን ? መልሱንና ፍርዱን ለአንባቢያን ትተነው እናልፋለን ።

እድርን ካነሳን ዘንድ ሌላው ሳንጠቁማቸው ልናልፍ የማንፈልጋቸው አንዳንድ ነጥቦች ይኖሩናል ። እነርሱም ከላይ እንደገለጽነው ሁሉ በአንዳንድ የሃዘን ቤቶች የሚታዩትና የሚሰሙት ጫጫታና ውካታ የሃዘን ቤት መሆኑ ተረስቶ ልክ የድግስ ቤት ከሚመስልበት ደረጃ ደርሷል ። እርሱም በድንኳኑ መካከል የእርስ በርስ ጭቅጭቅና ስለ



www.ethiopianorthodox.org

ማኅበራቸው ጥፋትና ልማት የሚወያዩት በሃዘኑ ጊዜ በመሆኑ ነው ። ማለትም በግል በስብሰባ ወቅት ተነጋግረው መፍታት የሚገባቸውን የግል ቅራኔም ሆነ ሂስና ግለሂስ በድንኳኑ መካከል ተቀምጠው ለቅሶ ደራሹም ሆነ ሌላው አስተዛዛኝ ጣልቃገብቶ ሲዳኛቸውና አስተያየት ሲሰጥ በጠቅላላ የሃዘኑን ቤት ግራ ሲያጋቡት በአብዛኛው ቦታ ይታያሉ ። ፀብና ጭቅጭቅ ሲበዛ ለማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ ይሆናልና ሊታሰብበት ይገባል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሴት እድር የሥራ ድልድልም ሆነ በኅብረት ሥራ ጊዜ የጓደኝነትና እንደ ቅርበታቸው ሥራውም የዚያን ያህል ቅርበትና ርቀት ይታይበታል ። የጓደኝነት ሥራ ሞቅ ደመቅ ያለ ሲሆን በጉርብትናና በአከባቢነት ብቻ ሆኖ ከመካከላቸው ጓደኛ የሌላት ከሆነች ግን እኩል ክፍላ ሥርታ በዚች ዕድርተኛ ቤት ድንገት ኀዘን ቢያጋጥም ብድሯ አይመለስላትም ይህም ጓደኛ እንዳላቸው ተረኞቹም ሆኑ መዳቢዎቹ ቸልተኞች ይሆናሉ ። ይህስ የሚገባ ሥራ ነው ? በኛ አስተያየት እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር መለያየትን ስለሚፈጥር ይታሰብበት እንላለን ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሥራ ላይ እንዳሉ



## የጤና ዓምድ

# የጨጓራ ሕመም

እነሆ መንገድህን የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ ማርቆስ ምዕ. ፩፥፪-፫ ።)

ጨጓራ በሰውነታችን ውስጥ ከሚገኙት የሆድ ዕቃዎች ጠቃሚ የሆነ ክፍል ነው ። በሰውነታችን ውስጥ የሚያከናውነው ተግባር እንደሚከተለው ነው ።

ህይወት ያለው ፍጡር ለመኖር መመገብ እንዳለበት የታወቀ ነው ። በተጨማሪም የተሟላ ጤንነት እንዲኖረን ምግብ ያስፈልገናል ። ስለዚህ የተመገብነው ምግብ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ጨጓራ ውስጥ ይገባል ። ከዛም በዚያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ (ጋስትሪክ ጁስ የተባሉ ፈሳሾች ከሆድ ግርግዳ ላይ በመመንጨት ምግቡን ቀስ በቀስ እንዲዋሐድና ምግቡ ከፈሳሹ ጋር በመቀላቀል ወደ ፈሳሽነት እስኪለወጥ ድረስ በሆድ ውስጥ ይቆያል ። ከዛ ወደፈሳሽነት ከተለወጠ በኋላ ወደ አንጀት ክፍል ይሄዳል ። ነገር ግን ከዛ ወደ ፈሳሽነት ያልተለወጠው ክፍል ግን ወደ ፈሳሽነት እስከሚለወጥ ድረስ አሁንም እዚያው ሆድ ውስጥ ይቀራል ይህ ሒደት በጤናማ አካል ከአንድ ሰአት እስከ ስድስት ሰዓት ይወስድበታል ። ሆድ ውስጥ የቀረው ያልተዋሐደው ክፍል ግን በሆድ ላይ በሚገኙት ጡንቻዎች መጨበጥ ኃይል አማካይነት ተጋፍቶ ወደ አንጀት ክፍል ይተላለፋል ማለት ነው ።

የጨጓራን ህመም ሊያመጡት የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ እነሱም ።

፩/ የምግብ አለመፈጨትና አለመዋሐድ

፪/ ብስጭት ንዴትና ጭንቀት

፫/ ከመጠን በላይ መብላት

ህመሙ በሚጀምርበት ጊዜ የሚያሳያቸው ምልክቶች አሉ ። የሆድ ህመም ይሰማል ። ህመሙ የሚጀምረው ብዙውን ጊዜ ምግብ ከተበላ በኋላ ነው ። ይህ ሁኔታ ሆድን በመንፋት በማቃጠል መልክ ነው ። እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ የምግቡ አይነት ቅባትነት ያላቸውን ምግቦች መመገብ ነው ። ምክንያቱም የቅባት ምግቦች በሆድ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የመቆየት ችሎታ አላቸው ። ስለዚህ ይህ ህመም ያለበት ሰው የቅባት ምግቦችን ከተመገበ ህመሙ ይነሣበታል በጨጓራ ውስጥ የሚፈጠረው የአሲድ ብዛት በጣም የጨመረ እንደሆነ ልብን የማቃጠል ኃይል አለው ሌላው ደግሞ የተፈጨውን ምግብ እንደገና ወደ ጉሮሮ በመመለስ ያቅራል ህመምተኛው የማቃጠል ሁኔታ ይሰማዋል ።

የጨጓራ ህመም ያለበት ሰው ህመሙ የሚሰማው በአንድ ቦታ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ጭምር ነው ለምሳሌ ያህል ።

፩/ ጨጓራ በላይኛው የሆድ ዕቃ ክፍል አማካይ ቦታ ላይ ህመሙ ይሰማል ከዛም በጀርባ በኩል በተለይም ከግራ ትከሻ ላይ ያመዋል ።

፪/ ደንዳኔም ። ይህ ቦታ የጨጓራንና የትንሹን አንጀት የሚያያይዘው ክፍል ነው ህመሙም ወደ ጀርባ በተለይም ከቀኝ የትከሻን በታች አካባቢ ህመም ይሰማል ።

፫/ የሐሞት ከረጢት በቀኝ በኩል በላይኛው የሰውነት ክፍል በጨጓራ በኩል ህመም ይሰማል ። ህመሙ ወደ ጀርባ እና ወደ ቀኙ ትከሻ ዝቅ ብሎ በመነራጨት ሰውነትን ይጐዳል ።

በሆድ ላይ የሚገኙት ጡንቻዎች ሳይታሰብ በሚኮማተሩበት ጊዜ በጨጓራ ውስጥ ያሉት ጥርቅሞች ማለትም የተባለው ምግብ በኃይል ተገፍቶ በምግብ ቧምቧ ይወጣል ። ከመውጣቱ በፊት ግን የማቅለሽለሽ ስሜት ይኖራል ።

በጣም ሃይለኛውና ቶሎ ሊድን የማይችለው ህመም የጨጓራ መቁሰል ነው ። ጨጓራ መቁሰሉ የሚታወቀው ከደም ጋር የተቀላቀለ ትውከት ሲያስታውከው ነው።ደም ሆድ ውስጥ ከቀረ ሔምግሎቢን የተባለው የደም ክፍል ወደ ቡናማ ይለወጣል ። ከዛም የትውከቱን መልክ በመቀየር ቡና አይነት መልክ እንዲኖረው ያደርጋል ።

እነዚህ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሦስት ምልክቶች ከሌሎች የጨጓራ ህመም ምልክቶች ጋር ሊገናኙ የሚችሉ ዋና ዋና ምልክቶች ናቸው ።

፩/ የምግብ ፍላጐት ማጣት

፪/ ምግብን መዋጥ አለመቻል

፫/ ምግብን በብዛት መብላት (የምግብ ፍላጐት ሲጨምር) እነዚህ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሦስት ምልክቶች (ህመሞች) የጨጓራን መድማት ወይም መቁሰል የሚያሳዩ ዋና ዋና ህመሞች ናቸው ።

፩/ ተቅማጥ

፪/ የሆድ ድርቀት

፫/ ጋስ

ህመምተኛው ማድረግ የሚገባው ነገሮች ፤

ህመምተኛው ህመሙ እስኪሚታገስለት ድረስ ምንም አይነት ምግብ መውሰድ አያስፈልገውም ። ነገር ግን ምግብ መውሰድ ከቻለ የላሙ ምግቦችን መውሰድ አለበት ።

በጣም ኃይለኛው የጨጓራ ህመም የሚነሣው አንዳንድ ጠንካራና አሲድ



www.ethiopianorthodox.org

ነክ ፍራፍሬዎችን አልኮል ነክ መጠጦችን የሚያቃጥሉ ምግቦችን በመውሰድ ስለሆነ በተቻለ መጠን ከነዚህ ነገሮች መራቅ አስፈላጊ ነው ። እንዲጋ

ጣሚ ከተወሰዱ እንኳን የሚያስታግሡ ነገሮችን ለምሳሌ ወተት እና የመሳሰሉ ጭማቂ መውሰድ ጠቃሚ ነው ።

ይህ በሽታ በሃገራችን የተለመደ ስለሆነ ምግቦችን በተቻለ መጠን በጥንቃቄ መውሰድ አስፈላጊ ነው ። ምክንያቱም በሽታው ከምግብ ጋር ግንኙነት ስላለው ነው ።

መድኃኒቶችንና ምግቦችን በተወሰኑ ሰአቶች መውሰድ አስፈላጊ ነው ። ሌላው ደግሞ ጭንቀትን እና የመሳሰሉትን ከሚፈጥሩ ነገሮች መራቅና መጠንቀቅ በጣም አስፈላጊ ነው ።

ሀመምተኛው ከጭንቀቱና ከንዴቱ እንዲወገድ የተለያዩ ጥሩ ጥሩ ምክሮችን መምከር እጅግ አስፈላጊ ነው ።

ተማሪ ነርስ መንበረ ምሕረቱ

## መድኅን ....

ከገጽ ፯ የዞረ

ይህውም ዓለም በኃጢአት በተንኮል እርስ በርሱም በመጨካከን ለአንተ ከማለትም ይልቅ ለኔ በማለት ወደ ጥፋት ሲያዘነብል ይታያል ። ለሰላም ከሚያወጣው ገንዘብ ይልቅ ለጦርነት የሚያወጣው ወጭ እሥር እጥፍ በመሆኑ ድኅነትንና ፡ በሽታን ፡ ድንቁርናን ፡ በመቃወም ፈንታ አንዱ ለሌላው መቅሰፍት በመሆን እልቂት በመፍጠር ፍቅር እየቀዘቀዘ ስለሄደ ጣፋጭ የነበረውን ዓለም መራራ አድርጎታል ።

በዓለም ሰላም እንዲበዛና መራራ የሆነው የሰው ልጅ ኑሮ እንዲጣፍጥ የመድኅን ክርስቶስን ልደት በመንፈሳዊ ስሜት እንድናከብር ያስፈልጋል ፡ ምክንያቱም በዓለም ላይ ብዙ የደስታ ለውውጦች እንደ ተደረጉ እናውቃለን የክርስቶስ ልደት ግን የሥጋን ብቻ ሳይሆን የመንፈስንም ለውጥ አስተባብሮ የያዘ በመሆኑ ምዕመናን ለሆን ሁሉ አዲስ ለውጥ ሆኖልናል ። ስለዚህ የክርስቶስን ልደት ስናከብር አዲስ ልብስን በመልበስ ብቻ ሳይሆን በአዲስ መንፈስ በአዲስ ልብ እናክብረው ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ከኢትዮጵያውያን ....

ከገጽ ፰ የዞረ

በታላላቅ በዓላት እየታጠኑ በክብር ይገኛል ።

የቤተ ክርስቲያኑ ታሪክ በተጠቀሱት ግብራት ይጠቃለላል ማለት ሳይሆን ለማስታወስ ያህል ነው ቤተ ክርስቲያኑ ከላይ እንደተገለጸው ጥንታዊና በርከት ያሉ ቅርሳቅርሶች የሚገኙበት ስለሆነ በይበልጥ ለመረዳት የሚፈልጉ ታሪክ ተከታታዮች ከቦታው ድረስ ሄደው ታሪኩን ተመልክተው በሰፊው ለመረዳት ይችላሉ ።

# የባህል ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነኝ በማለት እራሱን የሚያስተዋውቅ ሁሉ የእናት አገሩን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ፡ የዓየር ንብረትና የብሔረሰቡን የተለያየ ሥርዓተ ኑሮ ለማወቅ ካልቻለ ከሱ ብዙ ለመረዳት የሚፈልግ የውጪ ሰው በጠየቀው ጊዜ መደናገሩ አያጠራጥርም ።

ኢትዮጵያን ሀገራችንን ውብ ናት ከሚያሰኙአት ፡ የዓየሩ ንብረት ፡ የቦታዎቿ አቀማመጥ ፡ ነፋሻነቷ ፡ ተራራዋ ኰረብታዋ ከወንዞች ከሸለቆዎቿና ከፏፏቴዎቿ መጥቀስ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው ነው ። ታዲያ ከዚህም ጋር የሕዝቦቿ የተለያየ የአኗኗር ባህል (ጠባይ) ሲጨመርበት ተፈጥሮ ያደላት ውብ ሀገር የሚለውን ስም ሰጥቷታል ። ይኸውም የውጭ ቱሪስቶችን ዕለት በዕለት በመማረክ ላይ ከመሆኑም ሌላ ዋና መተዋወቂያዋ ደግሞ የብሔረሰቦች ባህልም ጭምር ነው ።



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማኅበረ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፥ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቊ. 116616
የመልእክት ሣ. ቊ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org